# እሰረኛው

… አሁንም፡ ያደረግካቸው ታላላቅ ተአምራቶች ለመሰማት፡ በጌታ በኢየሱስ ሰም፡ መጥተናል። እምነታችንን እንድትጨምርልን እንድትቀባንም፣ ዛሬ የጸለይነው ጸሎት እንደሚሰጠን አምነን፣ በታላቅ ጉጉት ቆመናል። አንተም እያንዳንዳቸው የሚጠይቁትን፡ በሙሉ ታውቀዋለህና። ጌታ ሆይ፡ ለእነዚህ ሁሉ እንጸልያለን፡ በተለይ ደግሞ ለሞት ሰለቀረቡት እንለምናለን። ሰላም ከሌላቸው ሰላምን ለነፍሳቸው ሰጥ። ለሰጋቸውም ፈውሰ ይሁን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

2 ጉባኤውን ባርክልን። ጌታ ሆይ፡ በዕሮብ ምሽት የጸሎት ጉባዔ፡ እንዲህ——እንጸልያለን፣ ይህም፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሆነን ብንሰበሰብ አንተ ከኛ ጋር እንደምትሆን አውቀን መሰብሰባችን ነው። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ቃልህን እንድትልክ እንለምንሃለን። አቤቱ ጌታ ሆይ፡ ተናገር፡ ልባችንን በልዩ፡ ደሰታ ይሞላ፣ ይህም ወደ ጌታ መምጣት እንደተቃረብን ሰለምናምን፣ ከፊታችን ለሚጠብቀን ታላቅ ቀን እንዴት በሰነምግባር መኖር እንድናውቅ ይረዳናል።

3 እምነት ማግኘታቸው የተለየ ጸጋ መሆኑን፣ እና የእምነት ትርጉም ሰለተረዱ ሰዎች እናመሰግንሃለን። በተጨማሪም ከፊታችን ባሉ ጉባኤዎች፡ ታላላቅ ነገሮች እንደምታደርግ፡ ሰላወቅን እናመሰግንሃለን። ጌታ ሆይ፡ እንደ ድሮው ዘመን፡ በጉጉት እንጠብቅሃለን፣ ይህም የሰማይን መሰኮቶች ከፍተህ በዚህ በመጨረሻው ዘመን አፈሰዋለሁ ብለህ እግዚአብሄር ሆይ የገባኸው ቃል የሚፈጸምበት ጊዜ መቅረቡ ሰለ አመንን ነው።

4 አሁንም ጌታ ሆይ፡ በምድር ሁሉ፡ ከሁሉም——ጋር፡ ትሆን ዘንድ እንለምንሃለን፣ እንደ ዛሬው ሁሉ፡ ብዙዎች በዙሪያችን በሁሉም ቦታ፡ ልመና እንዳላቸው ሰምተናል። ጌታ ሆይ፡ ልመናቸውን ሰጣቸው። አሁንም ታላቅ የእግዚአብሄር እጅ በምድር ሁሉ በሚፈልጉት ዘንድ ሲሰራ——ማየት ጸሎታችን ነው።

5 ኃጢአታችንን ይቅር በለን። ጌታ ሆይ፡ በመንፈሰህ እና በቃልህ ቅጣን፡ ይህም ሰውነታችንን፡ በሰነምግባር አንጸን፡ ታዛዥ ባርያዎች፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ታዛዥ አገልጋዮች እንድንሆን ይረዳናል። የጥንቶቹ ክርሰቲያኖች፡ የሠሩትን ሰራ፡ በልባችን ማሰብ እንድንችል እርዳን። ከአንተ ጋር በአካል የተገናኙ ሰዎች ሰናገኛቸው ምን አይነት ሰዎች ሆነው እናገኛቸው ይሆን። ፊታቸው በእምነት እና በደሰታ እንዴት ያበራ ይሆን። ሕይወታቸው ሕያው የእግዚአብሔር ቃል የነበረ ሳይሆን አይቀርም፣ በህዝብ መካከል ሲመላለሱ፡ “በሰዎች ዘንድ የሚነበብ ደብዳቤዎች ነበሩ።” እግዚአብሄር ሆይ፡ አሁንም አንድ ጊዜ ደግመህ ሰጠን።

6 ህይወታችን ለአንተ የተገዛ ይሁን፣ ይህም ጌታ ሆይ፡ መንፈሰ ቅዱሰ እራሱ በእኛ ውሰጥ መኖርያ እንዲያደርግ፣ እና በእኛ አልፎ እንዲናገር ነው። በየጎዳናው ሰንራመድ ከዓለም ጋር በክንዳችን ተሻሽተን ሰንተላለፍ፡ በሐሳባችን ውሰጥ፡ እንደነሱ መሆን፡ እንደማይገባን እንድናሰብ እርዳን። ጌታ ሆይ፡ መንገድ ለቀን

ትክክለኛ የምድር ስፍራቸውን፡ እንድንተውላቸው እርዳን። እኛ ግን ጌታ ሆይ፡ ወደ ስልጣን የምትመጣ መንግስት አለችንና። የሌላ ዓለም ልዑካን መሆናችን አውቀን፡ ከኋላ ወንበር መቀመጥ ይሁንልን። ታላቅ ንጉሳችን በቅርብ መጥቶ በግዛቱ ያሉትን መንግስታት ሁሉ ድል ይነሳቸዋል። ንጉስ ሆኖ ይገዛል፡ እኛም ከእርሱ ጋር፡ ምድር ላይ ሺ ዓመት፡ ከእርሱ ጋርም ለዘላለም እንነግሣለን።

7 ይህን በአእምሯችን ይዘን፣ ጌታ ሆይ፣ አሁን የጸሎታችንን መልስ በጉጉት እንጠባበቃለን። ንሰሓ እንገባለን። ታላቁን ፈቃድህ በመቃወም፡ ምንም ነገር ብንሰራ፣ ምንም ነገር ብንናገር፣ ወይም ምንም ነገር ብናስተምር፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያንጻን።

8 ምራን፡ ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ማታ አንዲት እህት፡ እሷ እና ባለቤቷ ወደ ቺካጎ እንጓዛለን ብላለች። ጌታ እምላክ ሆይ፡ ወደምትጠቀምባቸው ቦታ፡ ምራቸው፣ ይህም ጌታችንን ኢየሱስን ለማያውቁ በጨለማ ላሉ ለሌሎች፡ የብርሃን ጨረሮች ይሆኑ ዘንድ ነው። አሁንም ለታላቋ ቀን እንዴት እንደምንዘጋጅ እናውቅ ዘንድ፡ የተግሳጽ ቃልህ ለመስማት፡ ጉባኤውን አንተ እንድትቆጣጠረው፡ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

[በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። ወንድም ኔቪል አስተያየት ሰጠ—አርታዒ።]

ጌታ ይባርክህ። አመሰግናለሁ፡ ወንድሜ።

9 የእኔ እዚህ መገኘት እምብዛም ያልተጠበቀ ነገር ነው። አስቸኳይ ጥሪ ኖሮኝ ካልወጣሁ፡ በቀር፡ የጸሎት ጉባኤ እያለ፡ ቤት ሆኜ፡ በቤት ውስጥ ቁጭ ማለቴ፣ በጣም ቅር ይለኛል። መምጣቴ፡ ለእኔም ለቤተሰቤም፡ ድንገተኛ ነው፡ ሳንጠብቀው ዘው ብዬ ገባሁ። እንደደረስኩም፡ ወድያውኑ። "ወደ ጸሎት ጉባኤ እሄዳለሁ፡" ብያቸው ወደዚህ መጣሁ። እንደምመጣ ስለማታውቅ፡ ለመምጣት መዘጋጀት እንኳን ጊዜ አላገኘችም።

10 ሌላው በደቡብ ካሮላይና ወይም በሰሜን ካሮላይና ውስጥ የምትኖረው፡ እህታችን፡ ወንድማችንም ስለዚያ ብርሃን የሰጠችው ምስክርነት መስማቴ፡ እጅግ ደስ ብሎኛል። ግሪንቪል፣ ነው አይደል? [አንዲት እህት፦ "አይደለም። ሳውዘርን ፓይንስ ነው አለች።—አርታዒ።] ሳውዘርን ፓይንስ። አዎን።

11 ወንድም ሊ ቨይል ዛሬ እዚህ ነበር። በዛሬው ዕለት፡ በጥምቀት ስነ ስርዓት፡ ዛሬ አጠመቅኩት። ወንድም ሊ ቨይል፣ እዛ ከሚኖሩ አገልጋዮች አንዱ የሆነው፡ ወንድም ፓርከር ቶማስ፡ ታውቁታላችሁ። ማን ነበር...

12 ያኔ ትዝ ይለኛል—አንዲት እህት፡ ጥላ ነገር አጥሎባት። እህቴ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ወደፊት ለሚያደርግልሽ... እምነታችን ለመፈተሽ... የሌሎችንም እምነት፡ ማየት እንድንችል አንዳንዴ በራሳችን እንድንሄድ እንደሚለቀን ታላቅ ማረጋገጫ ነው። አንዳንዴ በቀጥታ ተመልክታችሁ፡ አንዳች ነገር አይታችሁ፡ ትናገራላችሁ፤ ሌሎች ግን ተመልክተው እያዩትም፡ ምንም ነገር የለም ሊሉ ይችላሉ። አያችሁ? ግን'ኮ አለ።

13 አያችሁ፡ በጳውሎስ ላይ የወረደው ብርሃን ማየት የቻለ አንድም ሰው አልነበረም፡ ብርሃኑ ግን በዚያ ነበር። ርግብ ከሰማይ፡ በብርሃን መልክ፡ በኢየሱስ ላይ ስትወርድ፡ ከዮሐንስ በቀር ያየ፡ ሌላ ሰው አልነበረም። ግን'ኮ በስፍራው ነበረ። አያችሁ?

14 እና ግን፡ የኋላ ኋላ፡ ይህ ብርሃን የእሳት አምድ ስለመሆኑ ለሰዎች ስነግራቸው፣ ማናቸውም ማመን አልፈለጉም። አሁን ግን የካሜራው ሜካኒካል አይን ቀርጾ ይዞታል።

አስተውሉ እርኩሰ መንፈስ ጨለማ ነው።

15 ልክ እንደ ህይወታችን ነው፡ ጥላዎች ነንና። እንግዲህ እኛ፡ ብርሃን ከሆንን፡ አካሄዳችንም፡ ህይወታችን ከቀኑ ብርሃን ጋር ከተዛመደ፡ በብርሃን ውስጥ እንጓዛለን።

16 ልክ ቀን ሲሆን፡ ወደ ላይ አይታችሁ "ፀሐይን አየኋት፡" እንደምትሉት ነው። በጸሐይ የሚወጣውን—ጥላ ታያላችሁ። የፀሐይ ነጸብራቅ ነው። የፀሐይ መኖር ያረጋግጣል እንጂ፡ እሱ ራሱ፡ ፀሐይ አይደለም። ፀሐይ መኖሩን ያረጋግጣል።

17 አሁንም እናንተ ማቀዝቀዣዎቻችሁ ይዛችሁ፡ በያላችሁበት ተቀምጣችሁ፡ ስትነጋገሩ ሳያችሁ፡ ይህ ማለት ህያዋን መሆናችሁ ነው፡ ይሁን እንጂ እናንተም የህይወት ጥላዎች ናችሁ።

18 ምክንያቱ፡ አንድ ነገር ጥላ እንዲፈጥር፡ በውስጡ ጨለማ ሊኖረው ይገባል። አያችሁ? ጥላ፡ ጥላ ለመሆን፡ በውስጡ ብዙ ጨለማ እና ብዙ ብርሃን ሊኖረው ያስፈልጋል። ሙሉ በሙሉ ጨለማ ብቻ ሊሆን አይችልም፡ ወይም ሙሉ በሙሉ ብርሃን ሊሆን አይችልም። ጨለማ ከሆነ'ማ እውነተኛ ጨለማ ነው። ብርሃን ከሆነም፡ ምንም ጥላ የለውም፡ ጥላ መሥራት የሚያስችለው ምንም ነገር የለውም። ነገር ግን ጨለማ ከብርሃን ጋር ከተቀላቀለ፡ ጥላ ይሰራል።

19 ስለዚህ የሌላውን ዓለም ህይወት እያንጸባረቅን ነንና። በእውነት የብርሃን ጥላዎች ነን። እንግዲያውስ ይህ ጥላ ብቻ ከሆነ፡ እናንተም፡ ክርስቲያን ከሆናችሁ፡ ሞት የሌለበት ሕይወት እንዳለ ያስረዳል፣ ምክንያቱም ይህ ሕይወት በውስጡ ሞት አለበትና። አያችሁ? የማየት፡ የማሰብ፡ የመንቀሳቀስ፡ የመናገር ችሎታ፡ ኖሯችሁ፡ በአምስቱ የስሜት ህዋሳት፡ የምትንቀሳቀሱ ህያዋን ናችሁና ይህ ጥላ ነው። እንደምታውቁት፡ እነዚህ፡ ሟቾች ናቸው። ብዙ ውጣ ውረድም አለባቸው። ታውቃላችሁ፡ ይህ ማለት... ነጸብራቅ ብቻ መሆኑ ነው፡ አያችሁ፡ የህይወት እና የሞት ውህደት ብቻ ናቸው።

20 ሥጋ ሁሉ ይሞታል። ነገር ግን በሟች ህይወታችሁ፡ የገነት ብርሃን የምታንጸባርቁ ከሆናችሁ፡ እንግዲያውስ፡ የዘላለምን ህይወት፡ ጌታን ታንጸባረቃችሁ። ከዚያ በኋላ ስትሞቱ፡ ወደዚያ ብርሃን መሄዳቹ የማይቀር ነው፡ ያንጸባረቃችሁት ነገር እሱ ነውና።

21 ከጨለማው ዓለም ከሆናችሁ፡ የምታንጸባርቁት ጨለማውን ነው፡ ፍጻሜአችሁም፡ ከጨለማ በቀር ሌላ አይሆንም። አያችሁ? ስለዚህ አሁን በነጸብራቅ እንገኛለን። ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ብርሃንንና ሕይወትን እንደሚያንጸባርቅ ሁሉ፡ ሞትም ጨለማን እንደሚያንጸባርቅ እናያለን።

22 ስለዚህ ሁለቱም አሉ። ነገ-... በሳምንቱ መጨረሻ፡ ምናልባት እሁድ፡ ትንሹን ፎቶግራፍ በማስታወቂያ ታቤላ እንዲሰቀል፡ በትልቅ መጠን አሳትመነዋል።

23 አስተውሉትም አታስተውሉት፡ እኔ አላውቅም እንጂ። እንደዚህ፡ **ስዕላችሁን** ታቤላ ላይ ይሰቀላል። እና ከዛ...

ከአንድ ሳምንት በፊት፡ በ—በወንጌል ስራ፡ ጃማይካ በነበርኩ ጊዜ... ቴፖችን በመላው አለም ልከናል። እና **ሰባቱ ማህተሞችን**... ወደ ጃማይካ ደሴቶች ዘልቀን፡ ወደ ውስጠኛው አገር ልከንላቸው ነበር። እና አካባቢው፡ ከብሉ ማውንቴን በስተጀርባ የሚገኝ እጅግ ኋላ ቀር አገር ነው። የአገሩ ተወላጆች—አንድ ሰው፡ እያዞረው የሚሰራ፡ መቅጃ አላቸው፣ በየጊዜው፡ እንዲህ—እያዞራችሁት፡ የሚጫወት—የድሮው ቪክትሮላ የሚባል፡ ቴፕ ነው። እና፡ በየደቂቃው አንድ ሰው መጥቶ፡ ሊያዞረው ያስፈልጋል።

24 እና ሰዎቹ፡ የቴፕ ቅጂውን የሚያጫውቱበት፡ አንድ—አነስተኛ ባለ ስድስት-ቮልት፡ ወይም ሌላ ዓይነት... ባትሪ ነበረቻቸው። እና፡ እንደሚመስለኝ—ዛሬ ማታ እዚህ እንዳለነው ስብሰባ፡ ሁሉም በአንድነት ሆነው፡ ስለ **ማሕተሞቹ** እያዳመጡ ነበር። እኔ እየተናገርኩ ሳለሁ፡ ወደ ክፍሉ ውስጥ፡የእሳት ዓምድ ሲመጣ፡ ሁሉም አዩ፡ የቴፕ መቅጃው ባለበት ቦታ ላይ መጥቶ በላዩ ላይ ተቀመጠበት። ካሜራውን አምጥተው ፎቶውን አነሱ። እና ልክ እንደዚህ አይነቱ፡ እዚያው፡ በላዩ ላይ መጣ። ስለዚህ አሁን፡ እናንተ እንድታዩት—በዚያ የማስታወቂያው ባነር ላይ፡ እንዲውለበለብ እያደርግነው ነው።

25 እግዚአብሔር ወደ እኛ... ወደ ዘመኑ ህልውናው ስላመጣልን ጸጋው አብዝተን እናመሰግነዋለን። አሁን ስለ ብዙ ነገሮች እናመሰግነዋለን።

26 እስኪ አሁን ደግሞ፡ ምናልባት የምናገርበት ርዕስ አገኝ እንደሆነ ለማየት፡ አንዳንድ ማስታወሻዎቼን ልፈትሽ። ወይም፡ እስኪ አንዳች—ነገር... በርግጥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፡ የተዘጋጀ፡ የሆነ ጽሑፍ ይዣለሁ። አንዱን ባገኝ፡ ምናልባት በምንጸልይበት ጊዜ፡ ጌታ የምናገረውን ነገር ይሰጠኝ ይሆናል።

አሁን፡ እሁድን በታላቅ ጉጉት እየጠበቅናት እንገኛለን።

27 በየስብከቶቹ እየተናገርኩበት ቆይቻለሁና። እና፡ እሁድ 'ለት፡ "ለምን ትጮኽብኛለህ? ህዝቡን ተናገር እና መንገዳችሁን ቀጥሉ፡" በሚል ርዕስ፡ ብዙ አቆይቻችኋለሁ።

28 አሁን ግን፡ ቀጣይ እሁድ ለበሽተኞች የሚጸለይበት የፈውስ ጉባኤ ነው። እና፡ ህመምተኞችን ስንቀርባቸው፡ እና ስንጸልይላቸው፡ ህመምተኞቹ ካልተፈወሱ፡ የሆነ ምክንያት ሊኖር ይችላል። ስለዚህ አንድ ነገር ማድረግ እፈልጋለሁ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እሁድ ማለዳ አጠር ያለች ስብከትም፡ ትኖረናለች። ከዚያ፡ የፈውስ አገልግሎት አደርጋለሁ፡ ለሰው ሁሉ ጸሎት አደርጋለሁ። ቢሊ ፖል ወይም ሌሎች፡ ስምንት ሰዓት ላይ፡ ቤተ ክርስትያን ሲከፈት የሚመጡትን ሰዎች፡ በር ላይ ሲደርሱ ወይም ወደ ውስጥ እንደገቡ፡ ካርዶችን ለማደል እዚህ ይገኛሉ።

29 ደግሞ፡ በዚያ ቀን፡ እንዲህ አደርጋለሁ፡ አንዳንድ ሰዎች የማይፈወሱበት ምክንያት ለምን እንደሆነ ጌታ የሰጠኝ አንድ እይታ እንዳለ አምናለሁ። ማስተዋልን ከማጣት የመነጨ እንደሆነ—አምናለሁ። እና እንደ ጌታ ፈቃድ፡ ምናልባት፡ በቀጣዩ እሁድ፡ በዚህ ርዕስ፡ እንነጋገራለን—ብዬ አምናለሁ።

30 ከዚያ፡ እሮብ ማታ የጸሎት ሰብሰባ አጭር ሰብሰባ ነው ሁላችንም፡ ሁሌም እንደምናደርገው፡ ተባብረን የምንጸልይ ይሆናል።

31 አንዳንዴ፡ በዚህ ዘመን እኔ—ከአስተዋልኳቸው ትልልቅ ነገሮች አንዱ፡ ስለምናምነው ነገር የልብ መስጠት ማነስ መኖሩ ነው። አያችሁ? አያችሁ? እግዚአብሄር፡ ዛሬ በዚህ ዘመን ያደረገው ነገር፡ በጆን ዌስሊ ዘመን፡ አድርጎት ቢሆን ኖሮ፤ በማርቲን ሉተር ወይም-በሌሎቹ ቢያደርገው፡ ምን ይሆን ነበር? በቤተ ክርስትያን፡ በመንፈሱ፡ እና በሳይንስ እና በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ የተረጋገጠ ስራ፡ ሲያደርግ እንደምናየው ሁሉ፡ ስለ—ስለ—ስለ ውህደቱ፡ እውቅና ልንሰጠው ይገባል። ገና ከመፈጸሙ በፊት የእግዚአብሄር ቃል ይናገረዋል ደግሞም ይተርከዋል። እንዲሁም እርሱ እንደተናገረው፡ ትንቢትን እየተናገርኩ፡ ከቦታ ቦታ ስንንቀሳቀስ፡ ልክ እርሱ እንዳለው፡ በትክክል ተፈጽሟል። እኛ ግን በሰንፍና እንደተሞላ ሰው፡ እስከ አሁን ድረስ ግራ በመጋባት ተቀምጠናል። “እንጃ ብቻ፡ ከእኔ የተነሳ ይሆን እንዴ? ወይስ፡ ከመላ—ቤተክርስትያን ይሆን እንዴ እላለሁ? ወይም—ወይም፡ ለመሆኑ እኔ እዚህ ውስጥ እኖርበት ይሆን እንዴ?” ምናልባት፡ እሁድ ጠዋት፡ በመጠኑም ቢሆን አብርሆት የሚሰጡን አንዳንድ ሐሳቦችን አነሰቼ ለመናገር እሞክራለሁ።

32 እና፡ ዛሬ፡ ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት፡ አንድ ነገር መጣልኝ፡ እና እዚህ አስፍሬዋለሁ። “ምናልባት፡ እኔ እዚያ ከደረስኩ በኋላ፡ ወንድም ነቪሌ፡ ‘ናና አገልግለን፡’ ብሎኝ ቁጭ ቢልስ?” ብዬ አሰብኩ፤ አያችሁ? “የተወሰኑ ቅዱስ ቃላት ብጽፍ ጥሩ ነው፡” ብዬ አሰብኩ። ምክንያቱም፡ እሱ፡ ተወዳጅ ወንድም እንደሆነ፡ አውቃለሁ፡ እኛም—እናመሰግነዋለን።

33 ስለ ቃሉ ከመጸለያችን በፊት፡ አንድ ወንድማችንን—እንኳን ደህና መጣህ ማለት እፈልጋለሁ። ስማቸውን ለመጥራት ያስቸግረኛል፡ ሁለት ናቸው። ወዳጆቼ ናቸውና፡ እዚህ አሉ። እና… በየቦታው፡ እየሄዱ የሚያገለግሉ፡ ወንጌላውያን እና አገልጋዮች ናቸው። መልዕክቶች በቴፕ ሰምተዋል። ሁለቱም ወጣት፡ ከተለያዩ የሐይማኖት ተቋማት የመጡ ናቸው። አንደኛው ወጣት፡ ቱሰን ድረስ፡ በበረራ መጥቶ፡ በቅርብ የነበረውን፡ ጉባኤ ጨርሶ ወደዚህ ለመድረስ፡ እጅግ ጓጉተዋል። በወንጌል ማሕበርተኞች ግብዣ ላይ ይመስለኛል። እና ይህ ጓድ፡ ወጣት ጓድ፡ መጣ። እና ከ…

34 ከካንሳስ የመጡ ናቸው። ይህ ሁሉ ርቀት ተጉዘው የመጡት እኔ እንዳጋባቸው ነው። ይህን ሳላደንቅ አላልፍም። እንደነዚህ፡ ገና ህይወት የሚመሰርቱ ወጣቶች እና ሰዎች፡ እግዚአብሔር ሰምቶ እንደሚመልስላችሁ፤ በጸሎታችሁ፡ ሲያምኑ ማየት ደስ ያሰኛል። እና እኔ እንዳጋባቸው፡ እንደ ኢንዲያና ግዛት ሕግ መሰረት የሚጠበቅባቸው ነገር ለማወቅ፡ ትናንትና እዚህ በደረሱ ጊዜ፡ ምንም እንኳን የደም ምርመራቸውን የያዙ ቢሆኑም፡ ከመጋባታቸው በፊት፡ በዚህ ግዛት ውስጥ፡ ሶስት ቀናት መቆየታቸው አይቀርም። ስለዚህ፡ እስከ እሮብ ጠዋት ድረስ መጋባት አይችሉም ማለት ነው።

35 እና ጥግ ላይ የተቀመጥከው ወንድማችን፡ ተነስተህ ሰምህን እና የተወደደቸውን እጮኛህን፡ እና ሁለተኛው ወንድማችን ጭምር፡ እንድታስተዋውቀን እድል ልስጥህ።

36 [ወንድማችን፡ “አመሰግናለሁ፡ ወንድም ብራንሃም። እዚህ በመምጣቴ ደስ ብሎኛል። ወንድም ሮጀር ኦ’ኔል እባላለሁ፡ ከካንሳስ፡ በወንጌል ስራ፡ ተጓዥ ነኝ፡ ‘በኢየሱስ ባለን እምነት፡ ኢየሱስ ያድናል፡ ይፈውሳል... ? ... ’ ብዬ በመናገር፡ ሁሌም እንደታጠቅኩ ነው... ? ... እሷ ፓትሪሺያ ብራውን ትባላለች፡ እጮኛዬ ናት። ዓርብ፡ እንጋባለን። መጨረሻ ላይ ያለው፡ ወንድም ሮኒ ሃንት ይባላል፡ የስራ-ባልደረባዬ እና የወንጌል-ባልደረባዬ ነው። እሷ ደግሞ ካሮል... ትባላለች፡ እጮኛው ናት... ? ... ዛሬ እዚህ በመገኘታችን እጅግ ደስ ብሎናል።”—አርታዒ።]

37 በጣም፡ እናመሰግናለን። እነዚህን ወጣት የጌታ ኢየሱስ አምባሳደሮች፡ በሄዱበት ሁሉ የሚያተጋቸው፡ የእግዚአብሄር በረከት፡ እንመኝላቸዋለን። እኔ እራሴ ከቦታ ቦታ እየዞርኩ የጌታን መምጣት እየተጠባበቅኩ፡ ክርስቶስን ለማገልገል በልባቸው ሸክም ያደረባቸው፡ ወጣት ወንዶች እና ሴቶች፡ እንዲህ ተነሳስተው ማየቴ፡ ደስ ይለኛል፡ አያችሁ። ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ፡ ወንድሜ፣ እህቴም።

38 አሁን ከዚህ በፊት፡ በህይወቴ ተናግሬባት ከማላውቅ አነስ ካለች መጽሐፍ እንከፍታለን። የፊልሞና መጽሐፍ፡ ልዩ የሆነች... አንድ ምዕራፍ ብቻ ናት። እንደው እኔ...

39 በመጠኑም ቢሆን አይርሽ ነኝና፡ በተጨማሪም—የኋላውን ጥንድ ጥርሴ ባሉበት ለማጠናከር፡ በታችኛው ጥርሴ ዙርያ ሽቦ ስለገባ። ኡ፡ አንዳንዴ፡ በትክክል የማውቃቸው ነገሮች፡ ስሞቻቸውን መጥራት ያቅተኛል። አንዳንዴ ደግሞ ትምህርት ካለመማሬ የተነሳ፡ በትክክል መጥራት ያቅተኛል። እና፡ አንድ ሰው ከኋላ አካባቢ “ፊልሞና፡” ብሏል፡ ትክክለኛ አጠራር ይመስለኛል።

40 ስለዚህ አሁን፡ አንድ ወይም ሁለት ቃል ከዚሁ ለማውጣት፡ ከ 1ኛውን ቁጥር።

**የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ፡ ጳውሎስ፡...**

41 ዛሬ እንደ ጌታ ፈቃድ፡ እኔ መጠቀም የፈለግኩት፡ **እስረኛው፡** የሚል አንቀጽ ነው።

42 ጳውሎስ ስለራሱ እንደ እስረኛ መቁጠሩ፡ ይገርማል። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ፡ ነጻ-ሆኖ የተወለደ ሰው ሆኖ፡ ስለራሱ ግን “እስረኛ” ብሎ ይጠራል።

43 ወደ ቆሮጦስን ሰዎች ሲጽፍላቸው፡ “ጳውሎስ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ሓዋርያ፡” ሲላቸው እናየዋለን። ሌላ ጊዜም፡ ወደ ጢሞቴዎስ፡ ወደ ተለያየ ስፍራ ሲጽፍ፡ “በእግዚአብሄር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ባርያ፡” ይላል። ለፊልሞና ሲጽፍለት ግን፡ “የክርስቶስ ኢየሱስ እስረኛ፡ ጳውሎስ፡” ይለዋል። “ሐዋርያው፡ ጳውሎስ፡” በሚል ርዕስ አንድ ቀን መሰበክ እፈልጋለሁ። “አገልጋዩ— ጳውሎስ፡” ብዬ፡ እሰብካለሁ። ሌላው ደግሞ፡ “እስረኛው፡ ጳውሎስ።”

44 ዛሬ፡ ግን፡ አንዱ ርዕስ ብዙ ሰዓታት ስለሚጠይቀን፡ ለዛሬ፡ “እስረኛው፡ ጳውሎስ፡” ልምረጥና፡ **እስረኛው፡** የሚል ርዕስ እወስዳለሁ።

አሁን ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

45 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ የዚህን መጽሐፍ ቅዱስ ገጾች፡ በስጋ ችሎታ፡ ሰው ሁሉ መግለጥ ይችላል፡ እንደ ተላከበት ብርሃን ትርጉሙን መግለጥ ግን የመንፈስ

ቅዱስ ብቻ ስራ ነው። ስለዚህ አሁን ይህን ታላቅ የሆነ ሰው፡ ታላቅ ነብዩ ጳውሎስ እራሱን፡ “እስረኛው፡” በማለት የጻፈበት ምክንያት፡ እንዲያስረዳን፡ እንድትመጣ እንጠይቃለን። አሁንም ስንጠብቀው መንፈስ ቅዱስ ይህንን ይግለጥልን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። ኣሜን።

46 ጳውሎስ፡ ይህን መልእክት፡ ለፊልሞና ሲጽፍለት፡ በከተማይቱ ማረሚያ ቤት ውስጥ፡ እ—እ—እስረኛ ሆኖ፡ በእስር ቤት ውስጥ አቀማመጡ ሳይቀር አስባለሁ። በዚህ ሁሉ፡ የቃሉ ትርጉም ምን ማለት እንደሆነ በትክክል የሚያውቅ ሰው ነው። በብረት መዝጊያ ተ—ተ—ተዘግቶበታል። ነጻ የሚያወጣው ሰው ካልመጣ ነጻ ሊሆን አይችልም። እስረኛ መሆን ማለት ምን እንደሆነም ጠንቅቆ ያውቃል። ሌላው ግን፡ በዋናነት፡ ሐዋርያው—በጥቂቱም ቢሆን... በወቅታዊው ሁኔታው ተመርኩዞ እንዳልጻፈው፡ ማለት በዚህ—እስር ቤት ውስጥ ተቀምጦ—የስጋውን መታሰር ማለቱ እንዳልሆነ እምናለሁ። ነገር ግን እርሱ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ነኝ ያለው—ስለ ሰብዕናው፡ ስለ—ስለ—መንፈሱ፣ ስለ ፈቃዱ እንደሆነ እምናለሁ።

47 ሁላችንም፡ ስንወለድ፡ የምንፈልገው ውሳኔ መወሰን እንድንችል፡ ነጻ የሰብዕናችን ውክልና ኖሮን ተወልደናል። እግዚአብሄር ራሱ በጽድቅ ያደረገው ነገር ነው። ምክንያቱ፡ እያንዳንዱን ሰው በአንድ አይነት ስሌት መምረጥ አለበት፡ ካልሆነ ግን... የመጀመርያውን ሰው በነጻ የሰብዕና ውክልና መምረጡ፡ በተሳሳተ መሰረት መርጦታል ማለት ነው። አያችሁ? እኛም ዛሬ፡ እንደ አዳም እና እንደ ሄዋን፡ አንድ ነን። ልዩነት የለንም። ትክክል እና ስህተት በፊትታችን ነው። ህይወት እና ሞት፡ ምርጫችንን ማድረግ እንችላለን፡ መምረጥ፡ የግል ጉዳይ ነው። አያችሁ?

48 የአዳም፡ እና የሄዋን ምርጫም ይህ ነው፡ ሁለቱም፡ የተሳሳተ—ምርጫ መረጡ። በዚህም ምክንያት፡ ዘራቸውን በሙሉ፡ የሰውን ዘር ሁሉ፡ ከሞት ስር፡ ለሞት ቅጣት አሳልፈው ሸጡት።

49 እግዚአብሄር ግን እራሱ በሰው አምሳል ወረደና ሞትን ለራሱ ወሰደ፡ የሞትን ቅጣት በሰውነቱ ከፈለ፡ ይህም... ነጻነት—የናፈቃቸው ባርያዎቹ ሁሉ በነጻነት እንዲመላለሱ ነው።

50 ስለዚህ አሁን፡ በአዳም እና በሄዋን ካደረገው አሰራር ውጪ፡ በሌላ መንገድ፡ እኛን ሊያስገባን ቢሞክር፡ “መዳን ብትፈልጉትም ባትፈልጉትም እኔ አድናችኋለሁ፡” ቢለን፡ የአዳም እና የሄዋን—የመረጠበት መሰረት ስሕተት ነበር ማለት ነው፡ አያችሁ። ነገር ግን ዛሬ፡ እኛ እራሳችን፡ ሞት ወይም ህይወት መምረጥ አለብን። ደግሞም እንችላለን።

51 እንደተናገርኩት፡ ብርሃንህ ከተረጋገጠ፣ ህይወትህ ከየትኛው ወገን መሆኑ ይታወቃል። ከየትኛው ወገን እኔ እንዲህ ነኝ ብትል ግድ የለኝም። የምታደርጉት፣ በየቀኑ፣ ምን እንደሆናችሁ ያረጋግጣልና። ድሮ ሲተረት “ሕይወትህ ይጮኻልና፡ ምስክርነትህን አልሰማውም፡” ይሉ ነበር። አያችሁ? ድርጊትህ—ይናገራል።

52 እኔ ሁሌም ቢሆን በመጮኽ እና በመዝለል የማምን ሰው ነኝ። እኔ ግን ሁሌ “ዓለም ይታዘብሃልና፡ ከኑሮህ በላይ አትዝለል፡” እልሃለሁ። አያችሁ? በኑሮአችሁ ልክ መዝለል ይገባችኋል፡ አያችሁ፡ የሚታዘብ ሰው አለ። ስለዚህ አሁን...

53 ብዙ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን አይመጡም። እንደው—እንደው፡ ብዙዎቹ፡ መምጣት አይፈልጉም። እና አንዳንዶቹ፡ ባይመጡም፡ ቅኖች ናቸው። ከቤተ ክርስትያን ጋር ህብረት ማድረግ እስኪጠሉ ድረስ፡ ብዙ ሙስና አይተዋል። እና ብዙ ጊዜ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ውኃ የማይቋጥር ነገር እንናገራለን፡ በነሱ ላይ መፍረድ አይቻልም፡ አያችሁ፡ ክርስትያን ነን እያሉ። ሰዎች በሚሆኑት ሰበብ—ህብረት ይጠላሉ። በዓለም ውስጥ ትልቅ እንቅፋት፡ ክርስትያን ነኝ እያሉ ያሉትን የማይመጥን ኑሮ የሚኖሩ፡ ወንዶች እና ሴቶች ናቸው። ይህ በትክክል እውነት ነው።

54 አሁን ግን፡ ጥርስ ማፋጨት በፍርድ ቀን ያገኛቸዋል። ልንገራችሁ፡ ሐጥያተኛ፡ እና ሰካራሙ፡ ቁማርተኛው፡ እና ዘማዊው ሁሉ፡ "ወደ ዘለአለም እሳት ሂድ፡" የሚል ፍርድ ሲነበብለት—ጥርስ አያፋጭም። አይበሳጭም። ነገር ግን እራሱን በቤተክርስቲያን ቅጥረኝነት በስተጀርባ ለመደበቅ የሚሞክረው ሰው፣ እርሱ በፍርድ ቀን ጥርሶቹን የሚያፋጨው እርሱ ነው። አያችሁ? ክርስትያን ነኝ እያለ፡ ሌላ ኑሮ የሚኖር ሰው። ይህ ሰው ቅጥረኛ ለመሆን ጀምሮ፡ ሌላ አይነት ህይወት ከሚኖር፡ ምንም ዓይነት ቃል መግባት ባይጀምር ይሻለው ነበር። ከባዱ እንቅፋት፡ አለ ቢባል፡ እኔ—ክርስትያን ነኝ—እያለ፡ ሌላ ኑሮ የሚኖር ሰው ነው።

55 ተአምራትን ለማድረግ ባለህ ኃይል፡ ምንጊዜም ህይወትህን አትመዝን። ወይም ባለን የቃል እውቀት እራሳችንን አንመዝንም። ነገር ግን መለሰ ብላችሁ ተመልከቱና፡ በራሳችሁ ላይ ዝርዝር ምርመራ አድርጉ ኑሮዬ ምን አይነት ፍሬ እያፈራሁበት ነው በሉ። አያችሁ?

56 4 ከዚህ በፊት፡ በፊኒክስ፡ አሪዞና በነበረ የባለአደራዎች ጉባኤ፡ ኢየሱስ የሚያንፀባርቅ፡ የክርስቲያን ሕይወት ነጸብራቅ የሚል ሰብከት ሰብኬ ነበር። ጨቅላ በነበርኩ ጊዜ፡ እጅግ ኋላ ቀር በነበረው፡ በኬንታኪ ግዛት እንደተወለድኩ እየተናገርኩ ነበር። እና እኛ—እዚህ—እንዳሉን አይነት—ቤቶች እና በቤቱ ውስጥ ሁሉ፡ ወይዘራዝርት ጸግጉራቸውን እና ሰውነታቸውን ለማየት፡ እንደሚጠቀሙባቸው፡ መስታወት፡ አይቶ የማያውቅ ልጅ ነው። ከቤት ውጭ በነበረው መታጠብያ ግን፡ ዛፍ ላይ የተጠረቀች፡ ትንሽ መስታወት፡ አባት እና እናቱ ታጥበው፡ ጸጉራቸው፡ ወይም ሰውነታቸው የሚያስተካክሉባት፡ ዛፍ ላይ የተጣበቀች፡ አነስ ያለች ሰባራ መስታወት ነበረቻቸው።

57 እውነት ለመናገር፡ ቤታችን እንደዚ አይነት ነበረች። ከልጆች መካከል፡ ማናችንም መስታወት ማየት ብንፈልግ፡ ሳጥን ሰበን፡ ወደ መታጠቢያው እንወጣለን፡ ከዚያ እራሴ፡ ከቆሻሻ ማጠራቅሚያ፡ ለቅሜ ባመጣኋት ሰባራ መስታወት—እናያለን። ይሄ ግን በኬንታኪ አይደለም። ኢንዲያና ውስጥ፡ እዚህ ኡቲካ ፓይክ ነው።

58 አሁን፡ ይህ ህጻን ልጅ እራሱን በዚህ መንገድ አይቶ አያውቅም ነበር። እና፡ ሴት አያቱን ለመጠየቅ፡ ወደ ከተማ፡ ወረደ። አያቱ ቤት ስለነበራቸው ክፍሎችን ሲጎበኝ በቤታቸው ውስጥ... በሩ ላይ ሙሉ መስታወት ነበረበት። እና፡ ህጻኑ ልጅ፡ ከአንዱ ክፍል—ወደሌላኛው ሲሯሯጥ፡ ፊት ለፊቱ ሌላ ልጅ አየ። ያየው ልጅም፡ እየሮጠ ነበር። ስለዚህ ጥቂት ደቂቃዎችን ቆም ልበልና ትንሹ ልጅ ምን እንደሚያደርግ ልየው ብሎ አሰበ። እና እሱ ሲቆም፡ ትንሹ ልጅም ይቆማል።

እራሱን ሲያዞር፡ ትንሹ ልጅ አሁንም እራሱን ያዞራል። እራሱን አከከ፡ ትንሹ ልጅም አከከ። በስተመጨረሻ፡ ምን መሆኑን ለማየት፡ ጠጋ አለ። እና ወደኋላው ዞረ። እናቱ በመገረም ታየዋለች፡ ሴት አያቱም እንዲሁ። "እንዴ፡ እማ፡ እኔ'ኮ ነኝ፡" አላት።

59 ስለዚህ እኔም፡"እኛ፡ እራሳችንም፡ የምናንጸባርቀው ነገር አለን፡" እላችኋለሁ። አያችሁ? ህይወታችን እየተንጸባረቀ ነው።

60 እና አሁን፣ በኖህ ዘመን ብንኖር ኖሮ፡ ከማን ጋር እንወግን ነበር? ኖኅ በኖረበት በዚያ ታላቅ ዘመን ምን ዓይነት አቋም ይኖረን ነበር? በሙሴ ዘመንስ ምን ዓይነት አቋም እንይዝ ነበር? በነቢዩ፡ ኤልያስ ዘመን፡ ዓለም ሁሉ—በታላቅ ጅምላ—እንደ ዘመናዊትዋ ኤልዛቤል በተናወጠ ጊዜ፡ የጌታን ባርያዎች ሁሉ ወደ ዓለማዊ ልማድ ጠራርጋ በወሰደቻቸው ጊዜ፡ ምን ዓይነት አቋም ይኖረን ነበር? ያኔ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ እና ካህናቱ ሁሉ ይሰግዱላት ነበር። አንጋፋ የመባል አቋም ትመርጣለህ፣ ወይንስ ከኤልያስ ጎን ጋር መሰለፍ?

61 ሌላው፡ ጌታችን ኢየሱስ በዘመኑ፡ የአለም ቀለም ያልቆጠረ፣ መርምረው እዚህ ትምህርት ቤት ገብቷል ሊሉት ያልቻሉ፡ በተጨማሪም—የካህናት ትምህርት ልምድ የሌለው፡ በማንም የማይታወቅ ሰው ነበር። "ከህጋዊ ጋብቻ ውጪ የተወለደ፡" ብለው—ስም አውጥተውለታል። ድንገት መጥቶ፡ ከዚህ በፊት ከሚያውቁት ትምህርት ሁሉ የተለየ ወንጌል መሰበክ ጀመረ። አገልጋዮቻቸውን እና ድርጅታቸውን፡ ሁሉ... እጅግ አወገዛቸው።

62 በዚህም ምክንያት ድርጅቶች ሁሉ—እንዲህ አወጁ፡- "ይሄን ነብዩ-ነኝ የሚለውን ሰው ለመሰማት፡ የሚሄድ ሰው ሁሉ፡ ከምኩራብ ይባረራል፡" በማለት የሰነ—ልቦና ሐጥያት የሆነው ሐሳብ አቀረቡ። ይህም ያስጠይቃቸዋል። ብቸኛው የመሰገጃ ቦታቸው በበጉ ደም ስር ነበር። እነርሱ ግን ወደዚህ መሰዋዕት መድረስ ይጠበቅባቸው ነበር። ስለዚህም—ውግዘት ነበረባቸው፡ ይህም የሚደንቅ ነው።

63 ይሄኛው ሰው ግን እንዲህ ያሉ ነገሮችን ችላ አለ። በሚያውቁት መንገድ ባይሆንም፡ ከቃሉ ጋር ፍጹም ሰው ሆነ። እናንተስ ከማን ጋር ትወግኑ ነበር? አያችሁ? አሁን፡ እናንተ... አሁንም መንፈሳችሁ ያንኑ መንፈስ ስለሆነ፡ አሁን የምትኖሩት ኑሮ ሁሉ፡ ያኔም እንዲሁ ማንጸባረቃችሁ የማይቀር ነው። አያችሁ? አሁን፡ ከእነርሱ ጋር ከወገናችሁ፡ ያኔም ትወግኑ ነበር። ምክንያቱ፡ አሁን በእናንተ ውስጥ ያለው መንፈስ ያኔም በሰዎች ዘንድ ነበረ።

64 ዲያብሎስ ከአንዱ ወደ ሌላው ይሄዳል እንጂ፡ መንፈሱን ፈጽሞ አይወስድም።

65 እግዚአብሔርም፡ ከአንዱ ወደ ሌላው ይሄዳል እንጂ፡ መንፈሱን ፈጽሞ አይወስድም። አያችሁ?

66 ስለዚህ፡ በኤልያስ ላይ የነበረው ያንኑ መንፈስ፡ ኤልሳዕ ላይ ወረደ፡ ያንኑ መንፈስ መጥምቁ ዮሃንስ ላይ ወረደ፡ እያለ ቀጠለ።

67 በክርስቶስ ላይ የነበረ፡ ያንኑ መንፈስ ቅዱስ፡ ደቀ መዝሙር ላይ መጣ፡ ከዚያም ቀጥሎ በህዝቡ ሁሉ ላይ ወረደ። አያችሁ ወይ? እግዚአብሔር መንፈሱን በፍጹም አይወስድም።

ስለዚህ ምርጫችንን ለማድረግ፡ እዚህ ላይ ተመስርተናል።

68 እና እኔ—እዚህ ጳውሎስ ሲጸጸት፡ በመታሰሩ ተጸጽቶ በምንም መልኩ ሲያዝን አላየሁትም። ስለ ራሱ ሲናገር ግን... ጳውሎስ ብዕሩን ይዞ ይሄን ደብዳቤ በጻፈ ጊዜ፡ እንዲጽፍ የገፋፋው፡ መንፈስ ቅዱስ እንደነበረ አምናለሁ። ይህም፡ ምናልባት እኛ ዛሬ፡ ከዚህ ጽሑፍ አንድ አንቀጽ አውጥተን፡ ጳውሎስ ለምን እንደዚህ እንዳደረገ፡ ማየት እንድንችል ነው። ምክንያቱም፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፣ መጽሀፍ ቅዱሳዊ የሆነ ነገርም ዘላለማዊ ነው። እዚህ ጋር፡ ጳውሎስ፡ አስከፊው እስር ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ፡ ለወዳጁ፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ፡" ብሎ፡ ለወንድሙ እንደጻፈለት አምናለሁ። ስለዚህ፡ በዙሪያው ያለውን ነገር በማየት ይሄን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል። ማለት፡ እስር ቤት ውስጥ ነበረ፡ ይሁን እንጂ—ለክርስቶስ ባርያ፡ ወይም አብሮት ለሚሰራ ሰው የነገረው ነገር፡ ይህ አይደለም። እሱ ያለው የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እስረኛ ነኝ ነው፡ ይህም ክርስቶስ እራሱ ደግሞ ቃል ነውና።

69 ጳውሎስም በዘመኑ ታላቅ ሊቅ የነበረ ሰው ነበር። ታላቅ ራዕይም ነበረው። ይህን ሰው—ያስተማሩት ሰዎች... ይህ ሰው፡ በዘመኑ በነበረ—ገማልያል በተባለ— ታላቅ አስተማሪ፡ እሱ ሊማርባቸው ከሚችሉት ታላላቅ ትምህርት ቤቶች አንዱ፡ በሆነው ሰፍራ የተማረ ነው። ለምሳሌ ያክል፡ እንደ እነ፡ ዊተን፣ ወይም ቦብ ጆንስ፣ እና የመሳሰሉ ታላላቅ እና ወሳኝ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው። እንደ—እንደ—የቃሉ አገልጋይ ለመሆን ተምሮ ነበር። ምናልባት አንድ ቀን ካህን፡ ወይም ሊቀ ካህን፡ እሆናለሁ የሚል ታላቅ ራዕይ በመያዝ በደንብ የተማረ ሊቅ እና ብልህ ሰው ነበር።

70 የራሱ ራዕይ ነበረው። እናም እነዚህን ሲፈልግ፡ የወሰዳቸውን ታላላቅ ስልጠናዎችን ለማሳካት፡ ዘመኑን ሁሉ፡ የጨረሰው፡ ምናልባት ከስምንት ወይም አስር አመቱ ጀምሮ፡ እስከ ሰላሳ ወይም ሰላሳ-አምስት ድረስ፡ ኮሌጅ ጨርሶ እስኪመረቅ ድረስ ህይወቱን በሙሉ በትምህርት አሳለፈ፤ ዲፕሎማዎቹን እና ሌሎቹን ሁሉ በመያዝ፡ በኢየሩሳሌም ባለው ሊቀ—ካህናትም ሳይቀር፡ በቁሳውስቱ መካከል በደንብ የታወቀ ሆነ። በግል የተጻፋ፡ ትዕዛዞችን፡ ከእሱ በመቀበል፡ ይህ እጅግ የታመነ ሳኦል፡ "እግዚአብሄር አምላክ ካዘዘው ትዕዛዝ ስርዓት ውጪ ሆነው እሱን የሚያመልኩ ሰዎችን እያደነ እያሰረ፡ ወደ ማረሚያ ቤት እንዲያስገባቸው ወደ ደማስቆ እንዲሄድ የታመነ ነው።" አስፈላጊ ከሆነ፡ ከፈለገም፡ እንዲገድላቸው ትዕዛዝ ተቀብሎ ነበር። እና... ታላቅ ራዕይ ነበረው።

71 አሁን ግን፡ የተማረው ትምህርት ሁሉ፡ እግዚአብሄር ጨርሶ ከውስጡ ወሰደበት። አያችሁ? የነበረው ራዕይ በሙሉ፡ አባቱ ያፈሰሰለት መዋዕለ ነዋይ በሙሉ፡ የእናትና አባቱ ህልም ሁሉ፡ እግዚአብሄር ሌላ የተሻለ አይቷልና—በርሱ ዘንድ የነበረ ፈጽሞ ተወሰደበት። ስለዚህ፡ በህይወቱ ዓላማዎች እስረኛ የነበረ ሰው፡ አሁን ግን፡ ቃል ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ሆነ።

72 ወደ ደማስቆ የሚወስደው መንገድ ጳውሎስን ለወጠው። ምናልባትም፡ ከቀኑ፡ አስራ አንድ ሰዓት፡ መንገድ ላይ ሳለ፡ እስኪወድቅ ድረስ ተመታ። ድምጽም፡- "ሳኦል፡ ለምን ታሳድደኛለ?" ሲለው ሰማ፤ አይኑን አንስቶ ተመለከተ። አይሁዳዊ ስለሆነ፡ እሻቅቦ አይቶ፡ የእስራኤል ልጆችን የመራቸው ጌታ እንደሆነ አስተዋለ፡ የእሳት አምድ መሆኑን ያውቅ ነበርና።

73 አስታውሱ፡ ይህ ሰው ነገሩን ተረድቶ ባይረካበት ዝም ብሎ “ጌታ፡” ኤሎሂም ወይም በካፒታል ኤል-ኦ-አር-ዲ ብሎ፡ ዕብራዊ ሆኖ ጌታ ብሎ ፈጽሞ አይጣራም፡ የተማረ ሰው ነውና። ወደላይ አሻቅቦ፡ ህዝቡን በምድረበዳ ላይ የመራ የእሳቱን አምድ ሲያይ፡ ብርሀኑን፡ ባየው ጊዜ፡ በካፒታል ኤል-ኦ-አር-... “ጌታ ሆይ፡ ማን ነህ? ” “ጌታ፡” ኤሎሂም፡ አለ፤

74 ሲያሳድደው የነበረው አካል፡ “እኔ ኢየሱስ ነኝ፡” ብሎ በመለሰለት ጊዜ፡ የነገረ መለኮት ምሁሩ እጅግ ሳይገረም አይቀርም። እንዴትያለ—ቅጽበታዊ ለውጥ ነው! አቤት! አቤት! ሰውየው ምን አይነት ከባድ ጊዜ አሳልፎ ይሆን፡ የነበሩት ምኞቶቹን ሁሉ፡ ሲመረምር፡ አሳዳጅ እንደነበረ፡ በቅጽበት ተረዳ። ምኞቱ ገፋፍቶት—ሊያደርገው ካሰበው ዋናው ነገር እጅግ አርቆታል። እና ሲያሳድደው የነበረው አካል፡ ሐዋርያውን፡ “እኔ ኢየሱስ ነኝ፡” “ለምን ታሳድደኛለህ? ” ባለው ጊዜ፡ ምን ያህል—ድንጋጤ ፈጥሮበት ይሆን።

75 ሌላ እዚህ ላይ ትንሽ አባባል ጣል ማድረግ እንችላለን። አያችሁ፡ በቤተክርስትያን ላይ ሲሳለቁ፡ መሳለቃቸው በኢየሱስ ላይ ነው እንጂ፡ ቀልዳቸው በቤተክርስትያን ላይ አይደለም። “ለምን ታሳድደኛለህ? ” ታዲያ ጳውሎስ፡ ከዚህ ሁሉ እውቀቱ ጋር፡ እሱ የሚያሳድዳቸው ሰዎች አገለግለዋለሁ ብዬ የምመካበት አምላክ ነው... ብሎ እንዴት ሊያምን ይችላል? እኔ እንደማስበው፣ ወደ ዝርዝር ጉዳዮች ሳንገባ፣ ምን ማለቴ እንደሆነ ለማወቅ ሁላችንም በደንብ የሰለጠን ይመስለኛል። ዛሬም ተመሳሳይ ነገር እየሆነ ነው።

76 እሱ ከሚያሳድዳቸው፡ ካልተማሩት፡ ይህንን ሰውን ጌታ አድርገው፡ በትህትና ከተቀበሉት ከገሊላ ሰዎች ይልቅ ጳውሎስ አብዝቶ የነቃ፡ በአለማወቅ ሁሉ እንኳን ብልህ እና የነቃ ሰው ነበር። ነገር ግን፡ ጳውሎስ፡ በታላቅ ትምህርቱ እና በአዋቂነቱ፣ ያንን ሊቀበል አልቻለም። በዚህ መንገድ የገጠመው ነገር፡ ምን አይነት ቅጽበታዊ ለውጥ ሆኖት ይሆን። ደግሞም ተልዕኮውን እንዳይፈጽም፡ በዕውርነት ተመቶ ነበር፡ ነገር ግን ወደ አንዱ ሰው ቤት... ቅን ወደሚሏት መንገድ እንዲሄድ ምሪትን ተቀበለ፡

77 ከዚያ በኋላ፡ ሐናንያ የተባለ ነብዩ፡ ነገሩን በራዕይ አይቶ መጣ፡ የት እንደተቀመጠ አይቶ ስለነበረ፡ መጣና፡ እርሱ ወዳለበት መጥቶ፡ ወደ ውስጥ ገባ። እርሱም እንዲህ አለው፡- “ወንድም ጳውሎስ፡ በመንገድ ላይ የተገለጠልህ ጌታ፡ አይኖችህ ማየት እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስም ትሞላ ዘንድ፡ እጆቼን እንድጭንብህ፡ ልኮኛል አለው።”

78 ያረፈበት ቦታ አውቋል። መቼም ለጳውሎስ—እጅግ ግርምትን ይፈጥርበታል! አያችሁ? አደርጋቸዋለሁ ብሎ የተማራቸው ነገሮች ሁሉ ተቃራኒ ሆነውበታል። ስለዚህ አሁን፡ የተማረው ትምህርት ሁሉ—ይዞ፡ ነገሩ—ባዶ ሆኖበታል።

79 ሌላው፡ ልምምድ ውስጥ እንደገባ ገብቶታል። አሁን ግን፡ ልምምድ ብቻ እንደማይበቃን፡ ጥሩ ትምህርት ሊሆነን የሚችል ሌላ ነገር ይህ ነው። ምክንያቱ ልምምዳችን በጌታ ቃል መሰረት ሊሆን ይገባል። ስለዚህ፡ ይሄን አይቶ፡ ታላቅ ነገር መሆኑንም ተረድቶ፡ በተጨማሪም፡ ከእሱ በፊት ይሄን የተቀበለ ሰው መኖሩን ስላወቀ፡ ወደ አረብ ምድረበዳ ወረደ—በዚያም ሶስት አመት ከስድስት ወር፤ በዘመኑ የነበረውን፡ የብሉይ ኪዳን፡ መጽሀፍ ቅዱስ—

በመያዝ፡ ይህ አሁን የተቀበለው ተሞክሮ፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ—በማነጻጸር፡ ትክክለኛነቱን ለመመርመር ወደ ምድረበዳው ወረደ።

80 እስኪ አሁን፦ “አይ፡ የሚገርም ቡጢ ነው፡” በማለት መንገዱን ቢቀጥልስ? “እውቀቴን—ብከተል ይሻለኛል ቢልስ”?

81 ስለዚህ አሁን፡ በአንድ ጉዳይ እሰር፡ እስረኛ ሊሆን የግድ ነው። ካነጻጸረው፡ እና ከአየው በኋላ፡ የዕብራውያን መጽሐፍ በጥላ እንዲህ መጻፉ አያስገርምም። አያችሁ? ሶስት አመት ከግማሽ፡ ከጌታ ቃል ጋር ጊዜ አሳለፈ፡ የጠራው አምላክ ወደ ኋላ መልሶ፡ እውቀቶቹን ሁሉ በመለዋወጥ ለመሆን የሰለጠነውን እና፡ ያሰበው ሁሉ፡ እየቀያየረበት እንደሆነ ተረዳ። ራዕዩን ሁሉ፡ ፈጽሞ ጠራረገበትና፡ እስረኛ ሆነ። የእግዚአብሔር ፍቅር፡ እጅግ ታላቅ፡ ከእርሱ ተርቆ የማይኖር—ልዩ መገለጥ ሆነለት።

82 ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኘ የእያንዳንዱ እውነተኛ አማኝ ተሞክሮ ያ ነው። ስለ ሌላው ነገር እስረኛ—እስኪያደርግህ ድረስ፡ ታላቅ ከሆነው… ነገር—ጋር—ሕብረት እንድታደርግ፡ ያደርጋል። አያችሁ? ለዚህ ነገር እስረኛ እንድትሆኑ፡ እናንተን ከሁሉ ነገር—ያርቃችኋል።

83 በአንድ ወቅት ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል፦ “መንግሥተ ሰማያት ዕንቁ እንደሚገዛ ሰው ናት። ባገኛትም ጊዜ፡ ታላቁን እንቁ ለመግዛት፡ ያለውን ሁሉ ይሸጣል።”

84 አሁንም እዚህ ያው ነው። አእምሯዊ ፅንሰ ሀሳብ—አላችሁ፡ የነገረ መለኮት ልምምድ አ—አ—አ—አላችሁ፤ እውነተኛ የሆነውን ነገር ወደ መፈለግ—በደረሳችሁ—ጊዜ ግን፡ ያላችሁን ነገር ሁሉ—ሸጣችሁ፡ ሙሉ በሙሉ ከዚህ ጉዳይ ጋር ትተሳሰራላችሁ።

85 ጳውሎስ—ልጓም እንደተደረገበት ገብቶታል። ለምን መሆኑንም አውቋል። ፈረስ—ላይ—ልጓም ሰናደርግበት፡ አንዳች ነገር—እንዲነትት ነው። እናም ጳውሎስ፡ ስለዚህ ልምምድ፡ እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር፡ ስለ ነበረው—የሶስት አመት ተኩል ልምምድ ሲጽፍ፡ እግዚአብሔር እንደመረጠው እና በመንፈስ ቅዱስ ልጓም እንደተጠመደ ተገንዝቦ፣ በሱ ዘንድ ባለው ልምምድ፡ ወንጌልን በአሕዛብ መካከል መሰበክ እንዳለበት አወቀ። መንፈሱ፡ ራሱ፡ ጠምዶታልና።

86 እና፣ ዛሬ፣ እኛም እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች፣ ታጥቀን፣ ተጠምደናል። መሄጃ የለንም። ከቃሉ ጋር ተጠምደን፡ በእርሱ ዘንድ ገብተናል። ማንም ሰው ምንም ቢናገር፣ ስለሱ በልጓም ተይዛችኋል። ልታመልጡት የማትችሉበት፡ የሆነ ነገር አለው። በመንፈስ ቅዱስ፡ ከቃሉ ጋር ታስራችኋልና፡ በዚህ ቀንበር ተይዛችኋል። እና ማንም ምንም ቢናገር፣ ቃሉ ነው፣ ሁሌም እንዲህ ነው። በመንፈስ፣ ለቃሉ፣ በእርሱ ታጥቆ፣ ከእርሱ ጋር በቀንበር ተይዞ፡ ተጣመረ።

87 ቀድሞ ከነበሩት ነገሮች—ልምዶቹ እና ራዕዩ፡ ከነዚያ ነገሮች፡ እንደተላቀቀ፡ በዚያ፡ በአረብ በረሃ ጀርባ ላይ፡ ትምህርቱን፡ ጨረሰ።

88 አሁን፡ ዛሬ፡ ማተኮር ያለብን በዚያ ነው፡ መጀመሪያ፡ መላቀቅ አለብን። ሰዎች ግን መላቀቅ አይፈልጉም። የሜቶዲስት ወንድም የሜቶዲስት አስተምህሮን በጥቂቱ ለማቆየት ይፈልጋል። አሀ-ታድያ። የባፕቲስት ወንድምም

የባፕቲስት አስተምህሮ በጥቂቱ ለማቆየት ይፈልጋል። እያችሁ? እናንተ ግን ከሁሉ በሙላት ተላቃችሁ፡ በአዲስ መንፈስ፡ ዳግም መወለድ አለባችሁ። ከዚያ በኋላ ግን፡ መንፈስ ቅዱስ ይምራ። ስለዚህ እንዲህ ማለት የለም፡- “እንዴ፡ አባቴ´ኮ፡ ታማኝ—አባል ነው፡ ወደ ቤተክርስትያን፡ ሲገባ፡ ከፓስተር ጋር ይጨባበጣል። አባቴ፡ መልካም ታማኝ አባል ነው።” ምናልባት ለዘሩ መልካም ሊሆን ይችላል፡ እኛ ግን ከሌላ ዘር ነን። እያችሁ? በዚህ ጊዜ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ዘመን መመለስ አለብን።

89 ካህናቶቹም፡ ተጠምደዋል። ነገር ግን እያችሁ፡ አሁን፡ ወደ ሌላ የዘመን ሙላት ሲሻገሩ፡ የተያዙበት አሮጌውን ልጓም ጥለው በአዲስ ልጓም ለመያዝ—መላቀቅ አልቻሉም።

90 ዛሬም የምናየው ተመሳሳይ ነገር ነው። በቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ፡ እና በመሳሰሉት እንደተረጋገጠው፡ በቤተ እምነት ዘመን ውስጥ አልፈናል፣ አሁን ግን መንፈስ ቅዱስ ራሱ ወርዶ ራሱን ወደሚያሳይበት፣ ራሱንም የሚገልጽበት፣ የገባውን ቃል ሁሉ፡ ወደሚፈጽምበት፡ ነጻ ዘመን ደርሰናል። ኦህ፡ ማይ! እንዴት ያለ መልካም ዘመን ነው!

91 ሌላ ነገር ደግሞ፡ ይሄን ያውቃል፡ በአንድ አይነት ቀንበር ባሉ ቦታዎች፡ መሄድ እንደማይችል… መሄድ ቢፈልግ እንኳ፡ መሄድ፡ እንደማይችል፡ ያውቃል። እንዲመጣ በተጋበዘባቸው ወንድሞች መካከል እንዲገኝ የራሱ ራዕይ እንደሳበው ያውቃል፣ በመንፈሱ ግን ሌላ ነገር ለማድረግ የሚገፋው ነገር ነበር። እሱ የራሱ አይደለምና።

92 ምናልባት አንድ ሰው እንዲህ ሊለው ይችላል፡- “ወንድማችን ሳውል፣ ወንድም ጳውሎስ፣ ቤተ ክርስትያናችን፡ እጅግ ትልቅ ነው፡ ወደዚህ እንድትመጣ እንፈልግሃለን። ትልቁ ጉባኤ የእኛ ነው። መባህ፡ ወዘተ እጅግ ይበረክትልሃል ሊሉት ይችላሉ።”

93 በመንፈስ ስለሚመራ ግን፡ “እዚያ ማዶ አንድ ወንድም አለ። ወደሱ ሄጄ ይህን ወንድም አድነዋለሁ፡ ወደ ጌታ እመልሰዋለሁ፡” ብሎ ያስባል። መንፈስ፡ ወደ ሌላ ቦታ እንዲሄድ፡ ይሞላዋል። እሰረኛ ነበርና። በትክክል።

94 አምላክ ሆይ፣ ከራስ ወዳድነት ምኞት፣ ከራሳችን ፍርድ እና ከተሻለ አስተሳሰባችን፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እሰረኛ እንድንሆን፡ እንደሱ አይነት እሰረኞች አድርገን። “የኢየሱስ ክርስቶስ እሰረኛ ነኝ፡” ሲባል፡ ደስ የሚል ሐሳብ ይመስለኛል።

95 ደግሞም ቃል ነው፡ ይሄን አትርሱ። እያችሁ? ማንም ምንም ቢያስብ ቃሉ ነው። እያችሁ? የቃሉ እሰረኛ ከሆናችሁ የትኛውም ቤተ እምነት ከሱ ሊያርቅህ አይችልም። እሱ—ቃል ነውና። አንተም… በቃ፡ እሰረኛው ነህ። እሱ እንደአሰራሩ መስራት አለብህ።

96 ስለዚህ አሁን፡ መሄድ እየፈለገ የማይሄድባቸው ቦታዎች ነበሩት፡ (ለምን? ) መንፈስ ስለማይፈቅድለት። ጳውሎስ፡ ብዙ ጊዜ፡ የሆነ ቦታ ለመሄድ ሲሞክር ታስታውሳላችሁ፡ “በጣም ጥሩ ጉባኤ ማድረግ የምችልበት ቦታ አለ፡” ብሎ ያስባል፤ መንፈስ ግን ይከለክለው ነበር። አሁንስ፣ ጳውሎስ እሰረኛ እንደነበር ይህ በግልጽ አያረጋግጥምን? የኢየሱስ ክርስቶስ እሰረኛ፡ በመንፈሱ፡ የቃሉ ምርኮኛ! ኦህ! ደስ ሲል። ኧረ-እህ።

97 እስር ነበር። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ እና ብቻ ለማድረግ፡ በፍቅር ማሰርያ፡ እና በሰንሰለት ተይዞ ነበር። እስረኛ ነበር። በፍቅር ማሰሪያ ውስጥ ነው። ከክርስቶስ ጋር በአንድ ቀንበር ውስጥ ነበረ። ከሌላ ግን ከማንም ጋር መጣመድ አይችልም። ከእርሱ ጋር ብቻ ተጣምዶ ነበር። ስለዚህ መሪው ወደ ሚወስደው ሁሉ፡ ይሄዳል። ግጦሽ መሬቱ፡ ምንም ያህል **በዚህ** እና **በዚያ** አረንጓዴ ቢሆኑም፡ መሪው እና ቀንበሩ በሄዱበት መንገድ መሄድ ነበረበት።

98 ኦህ፣ ዛሬ ማታ፣ እኛ፣ እንደ ብራንሃም ምኩራብ፣ ስለ ራስ ወዳድነታችን፣ ስለ ምኞታችን፣ እስረኞች ልንሆን፡ እና ከእርሱ ጋር እንድንጣመድ፡ ራሳችንን ሙሉ በሙሉ አሳልፈን መስጠት በቻልን። ሌላው ዓለም ምንም ቢያስብ፣ ምንምም ቢያደርግ፣ እኛ በፍቅር ማሰሪያዎች ተይዘናል፣ እስረኞች ሆነናል። “እግሮቼ እንዳይደንሱ፡ ስለ ክርስቶስ ታስረዋል። ዓይኖቼ ዘመናዊ እርቃን ሴቶች በመንገድ እንዳያዩ፣ ጭንቅላቴን እስካዞር፡ ድረስ፡ ዓይኖቼ ስለ ክርስቶስ እጅግ ተጠምዷል። ከአሁን—በኋላ፡ ይሄን ዓለም ላለማፍቀር፡ ልቤ ከእርሱ ጋር በፍቅር ቀንበር ተጠምዷል። ምኞቴ ምን እንደሆነ እንኳን እስከማላውቅ ድረስ ፈቃዴ ከእርሱ ጋር በጣም ተጠምዷል። በቃ፡ ‘አንተ ወደምትመራኝ ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ እከተልሃለሁ።’ እስረኛ እሆናለሁ።” አያችሁ?

99 ጳውሎስ በትክክል እስረኛ ነበር። ምንም የተሳሳተ ሐሳብ አልተናገረም። ቃሉን ለመጠበቅ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ እጅግ የሰለጠነ ሰው ነበር። ስለዚህ፡ እሱ በሌላ አካሄድ ተምሮ የነበረ ቢሆንም፡ እግዚአብሄር ግን—ሌላ አካሄድ አስተምሮታል። ምኞቱ ምንም ይሁን ምን፡ ጌታን እንዲጠብቅ በመንፈስ ቅዱስ ሰልጥኗል።

100 አሁን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ አንድ ነገር አሳያችኋለሁ። ተመልከቱ? አሁን አንድ ምሳሌ ብቻ እንጠቀማለን።

101 አንድ ቀን፣ ጳውሎስና ሲላስ፣ ሪቫይቫል በሚያደርጉበት በአንድ ከተማ ውስጥ በመንገድ ላይ ሲወርዱ። አንዲት ትንሽ ሴት፡ ጋኔን ያደረባት ሴት ተከትላቸው፡ እየጮኸች ከኋላቸው ትከተላቸው ነበረች። ጳውሎስ ግን እንደ ሐዋርያነቱ፡ ክፉውን መንፈስ ከሴቲቱ ውስጥ ለመገሰጽ፡ ስልጣን እንዳለው ማወቁ አያጠራጥርም። ነገር ግን አስተውላችኋል? ድንገትም፡ መንፈስ ቅዱስ፡ “ጊዜው አሁን ነው።” ብሎ፡ እስኪያዘው ድረስ፡ ከቀን ወደ ቀን፡ ይጠባበቅ ነበር።

102 አያችሁ? ጌታን መጠባበቅ ያውቃል። በስተመጨረሻ ግን “አንተ መንፈስ፡ ከእሷ ውጣ፡” በማለት አዘዘው።

103 እና ዛሬ ዛሬ ብዙ ሰዎች በትልቅ ራዕያቸው ተነሳስተው። በቃሉ ላይ ነቀፋ ያመጣሉ። እንደዚህ ባሉ ነገሮች ስንት ሪቫይቫሎች ከሽፈዋል፡ ምክንያቱም ወንጌላውያን ጌታ የሚናገራቸውን ለመስማት አይታገሱምና! አንዳንዶቹ—ማሕበራቸው “ሂድ፡” ብሎ ስለሚልካቸው፡ “ወደዚህ ና፡” ሲባሉ፡ ወድያውኑ—ይሄዳሉ። መንፈስ ቅዱስ ግን የተለየ ነገር እንዲሆን ይፈልጋል። ይሁን እንጂ፡ የሰውየው ራዕይ፡ በመንግስት የሚጠራ ካህን ወይ—ሌላ ነገር ለመሆን፡ ወይም ቄስ፡ ወይም ቢሾፕ፡ ወይም—መሆን የሚመኘው ነገር፡ “መሄድ አለብህ” እያለ ይጎትተዋል። ይሁን እንጂ፡ መንፈስ ቅዱስ፡

"**ወደዚህ** ሂድ።" ብሎ እንዳዘዘው፡ ያውቃል። አያችሁ? ለድርጅት ቀንበር እሰረኛ ሆኗል። ለድርጅቱ እሰረኛ ነው።

104 በክርስቶስ ቀንበር ከእርሱ ጋር ከተጣመረ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ይመራል። እሱ... ? ... አያችሁት? እሱ፡ በቀንበር ተይዟል፣ እሰረኛ ሆኗል። የሌላ ድምጽ እንደሚጮኽ ናስ—እና—እንደሚሿሿ ጸናጽል—ነው፤ ምንም ለውጥ አይፈጥርበትም። የሚሰማው የእግዚአብሄርን ድምፅ ብቻ፡ የሚናገረውም ሲመጣለት ብቻ ነው። ምንም አይናገርም።

105 አንድ ሰው፡- "ኦህ፡ ኦህ፡ ወንድም ጆንስ!" ወይም፡ ወይም፡ አንዳንዶቹ፣ ዛሬ በአገራችን ያሉ ታላላቅ ሰዎች፡ እንደነ ወንድም ሮበርትስ፣ ቶሚ ሂክስ፣ ወይም—ወይም—ወይም ኦራል ሮበርትስ፣ ወይም—ወንድም ቶሚ ኦስቦርን፣ ከእነዚህ ታላላቅ ወንጌላውያን ጥቂቶቹን። አንድ ሰው ቶሚን (ወይም ኦራልን።) "አንተ፡ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰው ነህ። እባክህ፡ ወደዚህ ተጋበዝልን፡" ቢል። "እኔ ደግሞ—እዚህ አሞት—ተሳሰሮ—የተኛ አጎት፡ ሰለ አለኝ። እና እሱ—አሞታል። እሱን ለመፈወስ የሚያስችል ሀይል አንተ እንዳለህ አምኛለሁና። እንድትመጣ እፈልጋለሁ እለዋለሁ።" አያችሁ?

ምናልባት ግን መንፈስ ቅዱስ "አሁን አትሂድ፡" ሊለው ይችላል።

106 ነገር ግን፡ ሰለ ጓደኝነታቸው፡ ከእሱ ጋር አብሮ የመሄድ፡ ግዴታ ይሆንበታል። ካልሄደ ግን፡ ለዚያ ሰው ጠላት ይሆናል። ሰውየው እንዲህ ይላል፡- "በጣም ጥሩ፡ ወደ ቤቴ ሳይመጣ፡ **እከሌ-እና-እከሌ** ቤት ሄደ። መሄዱን አውቄአለሁ። እኔ ለዓመታት፡ ጓደኛው ነበርኩ፡ እሱ ግን፡ ወደኔ ሳይመጣ የሌላ ልጅ ፈወሰ።"

107 ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር ከተጣመረ፡ እንዳይሄድም በመንፈስ ቅዱስ ቢገደድ፡ ባይሄድ ይሻለዋል። ጓደኛውን፡ ይውደደው። ነገር ግን ወደሱ ከመሄድ በመንፈስ ቅዱስ መመራት ይሻላል፡ ምክንያቱ ምንም ቢሆን፡ ጥሩ ነገር አይገኝበትም። ብዙ ጊዜ አጋጥሞኛል።

108 ጳውሎስ ግን "መንፈስን ጠብቁ፣" በማለት እንደተናገረ። የሚያደርገው እንዲነግረው መንፈሱን ጠብቋል። አንድ ቀን ሌሊት ቆሞ እየሰበከ፣ ወዲያ ወዲህ ሲል፡ አንድ አካል ጉዳተኛ ሰው አየ። ያን ጊዜም፡ መንፈስ ተናገረው፡- "እምነት እንዳለህ እያለሁ... " አለው፤ እንዴት? በደሴት ላይ ሲሄዱ፡ እንደሚሰባበሩ በተረዳበት በተመሳሳይ መንገድ። አያችሁ? "ለመፈወስ እምነት እንዳለህ እያለሁ። ኢየሱስ ክርስቶስ አድኖሃልና፡ በእግሮችህ ቁም።" አያችሁ? ይኸው። እሱ—ቀንበር—የተጠመደ ነበርና። ምንም ነገር ሳይከሰት ለአንድ ሳምንት ያህል ሪቫይቫል አካሂዶ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ እስኪናገር ድረስ ይጠብቀዋል። አያችሁ? ለዚያ ይግባኝ ተገዢ ነው።

109 አሁን "ወንድም ብራንሃም፣ እሁድ የተናገርከውን፡ ይህን ሁሉ ጊዜ ጠብቄዋለሁ ያልከንን ነገር እያወገዝክ ነው፡" ትላላችሁ።

110 በዚያ መንገድ ላይ፡ ያናገረኝ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እንደነበረ ግን አትርሱ፣ ሲናገረኝም፡- "እኔ ወደ ድውዮችና ወደ ህምተኞች እልክሃለሁ ብሎኛል።" አያችሁ? ለመንፈስ ቅዱስ መታዛዥ ነው። አዎን። እስኪያዘኝ ድረስ አንዳች አላደረግኩም። ነገር ግን **ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል** የሚል ቃል እስኪመጣልኝ፡ **ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል** እስኪመጣ ድረስ ጠበቅኩት።

አሁን፡ ልዩነቱ ይህ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ልዩነት፡ የሚፈጥረው፡ ይህ ነው። አዎን።

111 እሱ ግን የጌታን ቃል ጠበቀ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለማድረግ በመንፈስ እስር ሆነ፣ ከዚያም የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ ሆነ። ወዳጆች ሆይ፡ እስረኞች መሆን በቻልን!

112 ሞቃት እንደሆነ አውቃለሁ። ይሁን እንጂ ከፈቀዳችሁልኝ፡ ሁለት ተጨማሪ ገጸ—ባህርይ ማቅረብ እፈልጋለሁ። ወደ ስድስት ወይም ሰምንት ያህል ጽፌ ይዣለሁ። ይሁን እንጂ አንድ ወይም ሁለት ገጸ—ባህርይ መጥቀስ እፈልጋለሁ።

113 የሙሴን ገጸ ባህሪ እንውሰድ። እሱ ነፃ አውጪ ሆኖ የተወለደ ነው። ነጻ አውጪ—ሆኖ—እንደተወለደም ያውቅ ነበር።

114 ስለ ሙሴ ከመናገሬ በፊት ግን፡ ይህን ሐሳብ መናገር እፈልጋለሁ፡ ይህም፦ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ በእውነት ሊያገለግለው፡ እስረኛ ሊሆንለት የሚወድ ማንም ሰው ቢኖር፡ እንደሚጠቀምበት ነው። ሰው ግን እግዚአብሄርን ለማገልገል፡ መላ ማንነቱን እና ራዕዩን ሁሉ በመተው፡ አንዳች—ሳያስቀር፡ ህይወቱ፣ ነፍሱ፣ ስጋው፣ ፈቃዱ፣ ምኞቱ፣ እና ያለው ሁሉ፣ በማስገዛት፡ ቃል የሆነው፡ የክርስቶስ፡ ፍጹም እስረኛ ሊሆን ይገባል።

115 ከተሻለ ጥቅማችሁ በተቃራኒ መሄድ ሊኖርባችሁ ይችላል። ምናልባት፡ በአንድ ድርጅት ውስጥ፡ ሊያሳድጉህ እና አንተ የምትከብርበት ከፍታ ሊሰጡህ እንደሚችሉ፡ ልታስብ ትችላለህ። አንተ እራስህን ግን ምን ላይ ታገኘዋለው? እግዚአብሔር ለእሱ እስረኛ ለመሆን ፈቃደኛ የሆነን ሰው እስኪያገኝ ድረስ፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ እራስህን ተሸንፈህ ታገኘዋለህ።

116 እግዚአብሔር እስረኞችን ይፈልጋል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማረጋገጥ ትችላላችሁ። ከድሮ ጀምሮ ያደርገዋል። ሰው በማንኛውም ነገር ላይ፡ የክርስቶስ እስረኛ መሆን አለበት። ስለዚህ፡ ከክርስቶስ በቀር ከምንም ጋር ልትገናኙ አትችሉም፤ አባትህ፣ እናትህ፣ ወንድምህ፣ እህትህ፣ ባልሽ፣ ሚስትህ፣ ማንም ቢሆን። አንድነትህ ከክርስቶስ ጋር ብቻ፡ እና ከእሱ ጋር ብቻ ይሁን፡ ከዚያ ጌታ ሊጠቀምብህ ይችላል። እስከዚያ ድረስ ግን፡ አይሆንልህም።

117 አንዳንዴ ሰወጣ፡ ሰዎችን የሚከብዳቸው ነገር እናገራለሁ። አያችሁ? እንድትፈቱ—ለማድረግ እየሞከርኩ ነው። አንዳንዴ መጥፎ ልብሶችን ለብሰው ጸጉራቸውን የሚጨበርሩ ሴቶች፡ ወጥተው የክርስትና ህይወታቸውን እንደሚያስተካክሉ ሁሉ፡ እናንተንም ጅማሬ ሊኖራችሁ በግድ ያስፈልጋል። “ይህ’ማ ቀላል ነገር ነው፡” ትሉ ይሆናል። በጣም ጥሩ፡ መነሻ ሊኖርህ ግን ግድ ነው። ስለዚህ ከዚህ ሳትርቅ፡ እዚሁ በ ሀሁ ጀምር። አያችሁ? ከዓለማዊው ገጽታ ውጣ፡ እና፡ የክርስቶስ እስረኛ ሁን። እና ከዚያ ዝም ብለህ፡ የመጨረሻዋ መሰመር እስክትበጠስ ድረስ፡ ሁሉንም ነገር እየቆራረጥክ ቀጥል። ከዚያ—ከዚያ—በኋላ እስረኛ ነህ፡ ወጥመዱ ውስጥ ገብተሃል፡ በወጥመዱ—ውስጥ ይዞሃል።

118 አሁን ሙሴ፡ ነጻ አውጪ ሆኖ እንደተወለደ አውቋል። አስቀድሞ ተረድቷል። ሙሴ እናቱ ሞግዚቱ እንደመሆኗ መጠን፡ በዚያ በነገረችው መሰረት፤ የነበረው ራዕይ፡ አስተውላችሁታል።

119 ህጻኑ ሙሴ ከተወለደ በኋላ፡ ያለ ጥርጥር፡ እናቱ እንዲህ ሳትነግረው አትቀርም፦ "ታውቃለህ ሙሴ፡ እኔ እና... አባትህ፡ እምራን፡ ደጋግመን፡ በጸለይን ጊዜ። ነጻ አውጪው የሚመጣበት ዘመን መሆኑ፡ ከቃሉ አይተን፡ ተረድተናል። እኛም 'ጌታ አምላካችን ሆይ፡ ነጻ አውጪውን ማየት እንፈልጋለን፡' ብለን ጸለይን። አንድ ሌሊት፡ ጌታ በራእይ፡ አንተ እንደምትወለድ፡ እና ነጻ አውጪ እንደምትሆን ነግሮናል። ስለዚህ የንጉሱን ትእዛዝ አልፈራንም። ንጉሱ ለተናገረው ነገር ግድም አልነበረንም። ያኔ፡ አንተ፡ ሙሴ፡ ነጻ አውጪ መሆንህን ብናውቅም። አንተን ማሳደግ የምንችልበት መንገድ ፈጽሞ አልነበረንም።"

120 አሁን በግብፅ፡ አራት መቶ ዓመታት እዚያ እንደቆዩ፡ አስታውሱ። ገብቷችኋል?

121 "ትክክለኛው ነገር—ትክክለኛውን ትምህርት—ትክክለኛውን ስልጠና፡ እንድታገኙ፡ እንፈልጋችኋለን። ስለዚህ፡ እጃችሁን ይዤ ትንሽ ታምኳ ውስጥ ላሳፍራችሁና፡ ናይል ወንዝ ውስጥ ጉዞ እንጀምር። ጅረቱ ትንሿን ታንኳ በሸንበቆና በአረጎች መካከል፡ ብዙ ማይሎችን እየነዳት፡ ታች ድረስ አውርዶ፡ የፈርኦን ልጅ ወደ ነበረችበት፡ ገላ መታጠቢያ... ቦታዋ ድረስ ወደ ፈርኦን ቤተ መንግስት ማድረሱ፡ ምንኛ ይገርማል። ከዚያ በኋላም—የምታሳድግላት ሴት ሞግዚት መፈለጓን አውቃለሁ።"

122 በዚያ ዘመን፡ ህጻናት የሚያሳድጉባቸው ጡጦዎች፡ በርግጥም አለነበራቸውም። በዚህም ምክንያት—አዲስ አራስ መፈለግ ነበረባት። ስለዚህ...

123 "አሁን፡ ሚርያምን፡ ላክኋት። ቀርባ ቆመችና፡ እንዲህ አለቻት 'የምታጠባልሽ አራስ እኔ ላመጣልሽም እችላለሁ አለቻት፡' መጥታም እኔን ይዛኝ ሄደች። እና፡ ሙሴ፡ በሮቹ ሁሉ ተዘጋግቷል። የኔ ማር፡ አሁን አስራ ስድስት አመት ሆኖሃል፡ ደግሞም የፈርኦን ልጅ ልትባል ነው። አንድ ቀን ግን ህዝቡን ከዚህ እርነት የሚያወጣቸው ነጻ አውጪ ትሆናለህ አለችው።"

124 ከዚያ በኋላ የሙሴ ምኞቶቹ ማደግ ጀመሩ። "እሺ እማዬ፡ መማር እጀምራለሁ። የቻልኩትን ያህል ሁሉ እማራለሁ። ምን እንደማደርግ ታውቂአለሽ? ወታደራዊ ሰው እንዴት እንደምሆን አጠናለሁ፡ ከዚያ ህዝቡን እንዴት ማውጣት እንዳለብኝ አውቃለሁ። ታላቅ ጀነራል፣ ቢሾፕ፣ ከሆንኩ በኋላ፡ እንዴት እንደሚደረግ አውቃለሁ። ከዚያ በኋላ—አወጣቸዋለሁ። ኤልኤል ወይም ፒኤች/ዲዬን እመረቃለሁ። ከዚያ በሁላ—እሰራዋለሁ።"

125 ልክ እንደ "አባባ ቹኒኪ፡" መጻሕፍቶቹ ካነበባችሁ። እሺ። አባባ ቹኒኪ፡ "ፕሮቴስታንቶቹን ሁሉ እመልሳለሁ ብሎ፡" ለራሱ፡ ፕቶቴስታንት ሆነ። ስለዚህ፡ ከብዙ ዓመታት በፊት የነበረው "አባባ ቹኒኪ፡" የተባለው ቄስ፡ መጻሕፍቶቹን ገዝታችሁ አንብቧቸው። "አባ፡" ብለው ይጠሩት ነበር። በርግጥ እሱ፡ ወንድም ቹኒኪ፡ ነው። እኛ ማንንም ሰው "አባ፡" ብለን አንጠራም። እንደምናውቀው—የፕሮቴስታንት ሐይማኖት... ስህተት እንደሆነ በማሳየት፡ ሁሉንም ካቶሊክ አደርጋቸዋለሁ ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ይጀምራል። መጽሐፍ ቅዱስንም ሊያነብ በሄደ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስ ወረደና፡ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ። ከዚያ በኋላ—እራሱ ከእነርሱ አንዱ ሆነ።

126 እንግዲህ ይህን አስተውሉ፣ ሙሴ ሁሉንም ዓይነት ሥልጠና ወሰዷል። በጣም ብልህ፣ የተማረ፣ በጣም አስተዋይ! እንደነበረ—በደንብ አውቋል። ግብፃውያንን፡ እስከ ማስተማር... ድረስ። የሥነ ልቦና ባለሙያዎቻቸውን፡ ማስተማር እስኪችል ድረስ፡ የሚወዳደረው አልነበረም። ጀነራሎቻቸውን ወታደራዊ ስልት ምን ማለት እንደሆነ—እስከ ማስተማር ደረሰ። ታላቅ ሰው ነበር። ሰዎችም ሙሴን፡ ከታላቅነቱ የተነሣ ፈሩት። አቤት! እንዴት ያለ ሊቅ ሆነ! መሰላችሁ፡ ሊቀ ጳጳስ፣ ወይም ጳጳስ ነበር። ታላቅ ሰው ነበር። በተጨማሪም፡ ይሄን ለማድረግ የ—የ—የተወለደ መሆኑን ያውቃል። በታላቅ የግሉ ራዕይ፡ የሰለጠነ፡ ታላቅ ሰው ነበር።

127 ልክ እንደ ዛሬው። በእነዚህ ትምህርት ቤቶች፡ እየሰለጠኑ ያሉ ሰዎች፡ ለምሳሌ... አሁን፡ በምዕራብ፡ ያሉ የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ የአንድ-መቶ-ሃምሳ-ሚሊዮን-ዶላር የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት፡ ሊገነቡ ነው፡ አያችሁ፡ የ-... የአንድ-መቶ-ሃምሳ-ሚልዮን-ዶላር ትምህርት ቤት። እንደ'ኔ እንደ'ኔ፡ ለወንጌል ስራ ቢውል እላለሁ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ? የሚያደርጉትን፡ ስታዩአቸው፡ ተመርቀው ሲመጡ የሚሆኑት ነገር አይታችኋቸዋል? ምንድናቸው? የሪኪ ስብስባ ናቸው። ይሄ ነው። ሲወጡ የሚሆኑት ይህ ነው። ድሮም እንዲህ ነው፡ ሌሎቹም ያው ናቸው፡ ተመሳሳይ አካሄድ ነው። አያችሁ?

128 እና ሙሴን፡ በዚህ ሁሉ፡ ሰልጠናዎቹ፡ ሲሰለጥን፡ እናገኘዋለን፡ ዛሬም ቢሆን፡ ቢሾፕ፡ ታላቅ ሰው፡ እና ሌላሌላ በሚያደርጉን፡ ታላላቅ የሰልጠናዎች ምኞት፡ ምን ምን እናፈራለን? ራእዮቻችን ልክ እንደ ሙሴ ሆነውብናል። አያችሁ?

129 እግዚአብሄር ግን፡ ሰውየውን ከመጠቀሙ በፊት፡ ከራእዮቹ ሁሉ ያላቅቀዋል። ከሰልጠናዎቹ ሁሉ ሊያላቅቀው ያስፈልጋል።

130 ስለዚህ ወጥቶ፡ የነጻ ማውጣት ስራ ሰራ፤ አንድ ግብጻዊ ገደለ። እና፡ ከገደለ በኋላ ግን፡ እንደተሳሳተ አወቀ። ማድረግ አልነበረበትም። በዚህ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔርም ወደ በረሃ፣ ምድረ በዳ፣ ወደ ምድረ በዳ አወጣው።

131 ካስተዋላችሁ፡ በጣም የሚገርማችሁ፣ እግዚአብሔር መልእክት የሚልክባቸው ሰዎች፡ ወደ ምድረ በዳ ይወስዳቸዋል።

132 ጳውሎስን ሊያስለጥነው፣ ይህ ሁሉ ታላቅ ራእይ ምን እንደሆነ እንዲነግረው፣ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፡ ወደ ምድረ በዳ አመጣው። "ወደ አንድ በረሃ ውጣ አለው።" እግዚአብሔር የሚያደርገውን ሙሉ በሙሉ እስኪገልጽለት ድረሰም በዚያ ተቀመጠ።

133 በሙሴ ዘመንም፡ ሙሴን ወደ በረሃ ወሰደው። ሰነ መለኮትን እና ራዕዩን ሁሉ እስኪገፍለት ድረሰም፡ ለአርባ ዓመታት ያህል እዚያ አቆየው። ኦህ፡ ወደ ኋላ መለስ ብሎ ውድቀቱን ማየት የሚችልበት፡ ምን አይነት ድንቅ ጊዜ ነው። እኛም ዛሬ፡ ራዕያችን—ምን እንደሆነ ተገንዝበን፡ ተመሳሳይ ውሳኔ ማድረግ ይኖርብናል።

134 ፈውስን ለታመሙት ለማምጣት፡ እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ሁሉ ለማቃናት፡ ጌታ ከጥቂት አመታት በፊት፡ ያደረገው ነገር ካለ፡ የፈውስ መርሃ ግብሮቹን መለስ ብላችሁ መርምሯቸው።

135 እያንዳንዱ ሰው፡ እያንዳንዱ ድርጅት፡ በየድርጅቶቻቸው ሰለማያገኙ፡ የሚፈውሳቸው ፍለጋ ይወጣሉ። እኛስ ምን አደረግን? እስቲ ለአፍታ እንመርምረው። ሙሴ ያደረገው ያው አድርገናል። ወጥተን ተአምር መሳይ ነገር ለመሥራት ተግተን ተጉዘናል። "በሽታ እየሸተተኝ ነው። በእጄ ደም—ደም—ይታየኛል፡" ተአምር እንፈበርካለን። አያችሁ? እኛስ ምን አደረግን? አንዳንድ በእንደዚህ ዓይነት ከባድ ውጥረት ውስጥ የነበሩ የከሰሩ፣ አእምሮአቸው የታወኩ፣ ሰካራም የነበሩ ሰዎች፡ ሲፈወሱ ወደ ኋላ ተመልሰው፣ ከጴንጤቆሰጤ የመጣውን ትዕዛዝ አድርገው በማሰብ፡ እንደገና ድርጅቶችን እና ነገሮችን ወደመፍጠር ተመለሰዋል። አያችሁ?

136 እኛስ ምን አደረግን? አንድ ግብጻዊ ገድለናል። አዎን። ብዙ ሞክረናል። ተጨንቀናል። ዋጋ ከፍለናል። ደክመናል፣ ድምጻችን እስኪዘጋ ድረስ፡ ብዙ አዳሪ ጸሎቶችን ተሳትፈናል። ያልሆነ ነገር—ለመፈብረክ፣ የሆነ ነገር ለመቀባባት፣ እና ብዙ-አሸንክታቦችን ለማድረግ ሞካክረናል፣ ፍጹም ውድቀት ሆኖ አግኝተነዋል። ወደ ምድረ-በዳ መመለስ ያስፈልገናል። ትክክል። አዎን፡ ጌታዬ። መጋጋጥና እና ትግል። ለምን አታሰወግዱትም? ተመለሱ እና አሰወግዱት፡ አያችሁ፡ ይሄ ነው ማድረግ ያለባችሁ። ለምን፡ እነሱ ያደረጉትን ተመሳሳይ ነገር፣ ሙሴም ያደረገውን ተመሳሳይ ነገር አድርገናል። ምንም አይጠቅምም። ከአርባ አመታት በኋላ፡ የእግዚአብሄር ቃል እሰረኛ ሆኖ እራሱን አገኘ። ምን ለመሆን እንፈጋለን?

137 ዳግመኛ እንዴት መወለድ እንዳለብን፡ መንፈስ ቅዱስን እንዴት መቀበል እንዳለብን፤ ጥምቀት በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እንደሆነ፤ እና እግዚአብሔር የነገረን፤ እነዚህ ሁሉ እና የነዚህ ሁሉ፡ ታላላቅ በረከቶች መገለጥ በተሰጠን ጊዜ።

138 አያችሁ፡ ሰዎች፡ በዚያ ቃል ልጓም ተይዘው፡ ከመጠቀም ይልቅ፡ ምን አደረጉ? ቀድሞውንም ያልተሳካለት፡ የቤተ እምነታቸው ሰነ ሐሳብ ጀመሩ፣ እና እውነትን የሚመስል ነገር ለማምረት ሞከሩ።

139 እዚህ ጋር ባቆም ጥሩ ይመስለኛል። አያችሁ? ምን ማለቴ እንደሆነ ለማወቅ በቂ ጥበብ እንዳላችሁ እርግጠኛ ነኝ። አያችሁ? ግን፡ ለምን፡ ምን እንደተደረገ ተመልከቱ። እስቲ አሰቡት።

140 የእግዚአብሔርን መጻሕፍት በሚክዱ፡ በተደራጁ ሰዎች የተሞላ ህዝብ በቀር፡ ዛሬ—ዛሬ—ዛሬ ማታ፡ ምን አለን? የ—የ—የመንፈስ ቅዱስን ህይወት፡ "የ—የአእምሮ ጥንቆላ፡" ብለው የሚጠሩ ሰዎች፣ እንደነዚህ ያለውን ነገር ወደ ቤተክርስቲያናቸው እንዳይገባ የሚከለክሉ፣ ሰለ እባቡ ዘር፣ ሰለ ዘላለማዊ ደህንነት እና መንፈስ ቅዱስ ሰለ ገለጠው፣ ቃል መሆኑ ሰለተረጋገጠው ነገር አንዳች እንድትጠቅሱ አይፈልጓችሁም። መጥተው ስህተት መሆኑ ማሳየት ከቻሉ ብዬ፡ ደጋግሜ ዕድል ሰጥቻቸዋለሁ።

141 ምን ተገኘባቸው? ሉተር እና ሌሎች፡ የነበራቸው ያው ተመሳሳይ ነገር፡ አያችሁ፡ ግብጻዊ መግደል ብቻ። ምን አይነት… ምንድነው? ምናልባት አንድ ሰው መሰረቅ እንዲያቆም፡ ወይም ለሚስቱ ታማኝ እንዲሆን… አድርገውት ይሆናል። ከዚያስ ምን አደረጋችሁት? የቤተ ክርስቲያናችሁ አባል። "ናና አባላችን ሁን።" አይደል?

142 አርባ አመት ከወሰደው ስልጠና፡ ድሌ ብሎ ሊጠቁም የሚችለው ብቸኛው ፍሬ፡ ወድቆ የበሰበሰው ሬሳ፤ ወድቆ የበሰበሰው፡ የሞተ የግብጻዊው ሬሳ ብቻ ነው።

143 የዛሬም ከዚህ የዘለለ አይደለም። እኛም ሰራን (የምን-ለው) የምንመካበት ብቸኛው ተሻጋሪ ሪቫይቫል፡ ሆተንቶት ስለ ግብጽ የሚያውቀውን ያህል ስለ እግዚአብሄር ምንም እውቀት የሌላቸው የበሰበሱ የቤተ ክርስትያን አባላት ብቻ ናቸው። ትክክል ነው። አንዱ ይመጣና፡ የእግዚአብሄር ቃል ሲነግራቸው፡ “እኔ ይሄን አላምንም፡” ይላሉ። “አንተ የምትለኝ ነገር አልቀበለውም፣ አላምነውም፡” ይላሉ። እያችሁ? ገባችሁ? ከዚህ ሁሉ ዉጣ ውረድ እና ድካም በኋላ፡ እጃችንን የምንጠቁምበት ይሄ ከሆነ እጅግ ይሰቀጥጣል።

144 ምናልባት አንድ ትልቅ ትምህርት ቤት ልንጠቁም እንችላለን፡ ይሁን እንጂ ሙት ነው። ድርጅት ልንጠቁም እንችላለን፡ የሞተ ነው። ይሸታል። መጀመርያ መንጭቀን እንዳመለጥነው አይነት ነገር ነው። ወደ ኋላ ስንመለከት ግን “ውሻ ውደ ትፋቱ፡ እርያም ወደ ጭቃው፡” እንደሚሉት ነው። አንድ ሙት ግብጻዊ።

145 አንድ ሰው መጥቶ ሙሴን፦ “ከእንግዲህ፣ ስለ ሕዝቡ፡ ምንም አይሰማህምን? አንተ’ኮ ይህንን እንድታደርግ ተጠርተሃል።” ሙሴ ለዚያ እንደተጠራ፡ የሚያውቅ አንድ ሰው። “እንዴት ነው... ስለ ህዝቡ ማሰብ ተውከው’ዴ? ”

“አይ፡ አልተውኩትም።”

146 “ታድያ፡ እንዴት ወጥተህ፡ **ይሄን** አታደርግም? እንዴትስ ሄደህ፡ **ይሄን** አትሞክርም? እና ለምንስ ከሌሎቹ ጋር አትስማማም? ”

147 ሙሴ የጌታ ቃል የሚታወጅበትን ልምምድ፡ በቁጥቋጦው እስኪያገኘው ድረስ፡ እየተገፈፈለት በዚያ ቆየ። “**እኔ** የአብርሃም፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ አምላክ ነኝ። ቃል ኪዳኔንም አስቤአለሁ። አሁንም ላድናቸው መጥቻለሁ። እንድትሰራውም አንተን እልክሃለሁ።” ይሄው ነው።

148 ያየው ቃሉን ነው እንጂ፡ የህዝብን ፍላጎት ወይም ምኞት አልነበረም። ከዚያስ ምን ሆነ? ከዚህ በኋላ ግብፃውያንን መጋፈጥ አልፈለገም። ከዚህ በላይ ይህን ነገር መጋፈጥ አልፈለገም። ነገር ግን እስረኛው ሆነ። ኣሜን። በአርባው ዓመት ስደት፣ እየተራቆተ ቆየ፣ ከዚያ በኋላ ግን፣ ኃያሉ ሙሴ ከነሙሉ ሊቅነቱ፡ በሚቃጠለው ቁጥቋጦ እስረኛ ሆነ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሴ፡ በቃልም ሆነ በሥራ በግብፅ የበረታ ኃያል ሰው እንደነበር ይናገራል።

149 ኃያሉ የነገረ መለኮት ሊቅ ግን በሚቃጠል ቁጥቋጦ ፊት ምን ያደረገውን ተመልከቱ። አለመቻሉን ብቻ ተናዘዘ። እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ሲመለከት፣ ይሄን የማድረግ አቅም እንደሌለው ተናዘዘ። ሆኖም፣ ሊሰጡት በሚችሉት ሰነ መለኮት ሁሉ፣ በምርጥ ትምህርት ቤታቸው የሰለጠነ ነው። ሆኖም፡ ግን፡ የእሳቱ አምድ... በቁጥቋጦው ላይ ወርዶ እያየ ምን ማድረግ ይችላል? “እረ-እንደው፡ እኔ አፈ ትብ ነኝ። ጌታ ሆይ፡ እሄድ ዘንድ፡ እኔ ማን ነኝ? ” አለ። እያችሁ?

150 “ሙሴ፡ ከአንተ ጋር እነጋገራለሁና። ጫማህን ከእግርህ አውጣ። እራስህን እራቁት አድርግ፡ ጫማህ ጭምር። እንደገና ምድር ላይ—ባዶ ሁን። ልናገርህ እፈልጋለሁ።”

151 ማውራት እንኳን አልቻለም። በመጨረሻ፡ ልክ ጳውሎስ እንደ ተመረጠ፡ የተመረጠ እስረኛ፡ የተመረጠ ነቢይ ሆነ። ሙሴ የተመረጠ፡ ነፃ አውጪ ሆነ። በስተመጨረሻ፡ እግዚአብሔር የመረጠውን ተገዥ ለእሱ እስረኛ አደረገው። ኦ፡ ሃሌሉያ! የሚንቀሳቀሰው የእግዚአብሄር ቃል ሲያንቀሳቅሰው ብቻ ሆነ። “ማን ላከኝ ልበላቸው? ”

“እኔ ነኝ።”

“እንዴት አደርጋለሁ? ”

“እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ።”

152 “እሺ፡ ጌታ ሆይ፡ እንዳልክ ይሁን። እነሆኝ።” ኦህ፡ ማይ! በቃ፡ እስረኛው ሆነ።

153 ጸረ አስተሳሰቡ መሄድ ጀመረ። ከዚህ በፊት፡ ሰራዊት እንድያዝዝ የተማረ ሰው። “ሰይፍህን፡ አንሳ! ወደ ፊት-ሂድ!” “ሰረገሎች፡ ቦታ ቦታቸውን ይያዙ! ጦራችሁን፡ ወደፊት! ተዋጉ!” ለማለት የሰለጠነ ሰው፤ ድል ለመንሳት እንዲህ ይወጣ ነበር። ሰልጠናው ይህ ነበር።

አሁን ግን “ምን ይዤ እወጣለሁ? ” አለ፤

“በእጅህ ምን አለ? ” አለው፤

154 “ብትር።” “ዱላ።” እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ለሰው አእምሮ አሰቂኝ ነገሮችን ያደርጋል። ገብቷችኋል? ዱላውን በእጁ ያዘ። ሪዙ ተንጠልጥሏል። ሰማንያ ዓመቱ ነው። ሚስቱ በበቅሎ፡ ልጁም ዳሌዋ ላይ ጭኖ። ትንሽ፣ አርጅተው የተንጠለጠሉ ክንዶቹ፡ በትር ይዟል። **ጌታ ሰራዊት እንዲህ ይላል** የሚል ቃል ሰለያዘ፡ እራሱን ቀና አርጓል። ለምን? በስተመጨረሻ መልህቁን አጠናክሯልና።

155 “ቃሉ ሲያንቀሳቅሰኝ ብቻ እንቀሳቀሳለሁ። ቃሉ ከተናገረኝ ብቻ እናገራለሁ።” በቃ እስረኛ ሆነ።

ወዴት ነህ?

156 “አንድ ተልዕኮ ይዣለሁ፤ እግዚአብሄር የላከኝን ነገር፡ በዚህች ብትር፡ ፈርኦንን ለማሳየት በፊቱ እቆማለሁ።” አሜን።

“ከዚያ በኋላስ ምን ልታደርግ ነው? ”

“ይህን ካደረግኩ በኋላ፡ የሚቀጥለውን ነገር እሱ ያዘጋጃል።”

157 ይሄ ነው። ዛሬ ማታ፡ ከአንተ የሚጠበቀው አንድ ነገር ብቻ ነው፡ መጀመርያ፡ ተማረክለት፡ እስረኛው ሁን። ስለ ራስህ ወይም ስለ ሌላ ነገር አታስብ። እስረኛው ሁን።

158 ሙሴ እስረኛው ሆነ፣ መናገር እንኳን እንደማይችል ተናዘዘ። በስተመጨረሻ፡ እግዚአብሄር እጁን በያዘ ጊዜ፡ ወደሚያንቀሳቅሰው ሁሉ የሚንቀሳቀስ ሆነ። ወዴት፡ ቃሉን ነገረው። ቃል መሆኑን አወቀ፡ እራሱንም ለቃሉ

ታዛዥ አደረገ። መንፈስ ቅዱስ፡ ጌታ ራሱ፡ ሙሴን ስለ እግዚአብሄር ፈቃድ በልጓም ይዞታል።

159 በጳውሎስ ላይ ያደረገውም ተመሳሳይ ነገር ነው። ልክ ነው? ጳውሎስን በልጓም አሰረው፡ አጭር፡ ባለ ቆልማማ-አፍንጫ፣ ሰላቅ አይሁዳዊ፡ አቤት መዓርጉ ፒኤች/ዲው/፡ አቤት ኤልኤል/ዲ/ ሁሉ። ሲናገር ግን “ስለ እግዚአብሄር ቃል የሚሰቃየው መከራ እኔ አሳየዋለሁ፡” ብሏል። አያችሁ? እሱም...

160 ከዚያ በኋላ ጳውሎስ ቁጭ ብሎ የእግዚአብሄርን ቃል አይቶ፡ ኢየሱስ መሆኑ ከተረዳ በኋላ፡ እጆቹን ወደ ላይ ከፍ አደረጋቸውና ስለሱ እስረኛ ሆነ። “በአሕዛብ ፊት ስሜን ይሸከማል።” የእግዚአብሔር ፍቅር ከቃሉ ጋር አቆራኘው። ከዚያ ወጣ።

161 “ሙሴ እኔ የአባቶቻችሁ አምላክ ነኝ። እኔ የአብርሃም፣ የይስሐቅ እና የያዕቆብ አምላክ ነኝ። ቃል እንደገባኋቸው አሰብኩ፣ የሕዝቤንም መከራ አይቻለሁ። አሁንም የተሰፋው ቃል ጊዜ ደረሰ። ቃል ኪዳኔን አሰብኩ። አንተም ቃሉን ታውቀዋለህ። ስለዚህ አንተን በልጓም ላጠምድ ወርጃለሁ። እንድትወርድልኝ አጥምጄሃለሁ፡ ወርደህ ህዝቤን ከባርነት ነጻ እንድታወጣልኝ፡ በኃይል አጠመድኩህ። በእርሱም ተአምር አሳይሃለሁና፡ ያን ብትር ለምስክር፡ በእጅህ ያዝ።” ዳዊትን፡ በወንጭፍ እንደተጠቀመበት። አያችሁ?

162 በልጓም፡ ተጠምዶ፡ ወረደ። በመጨረሻም እግዚአብሔር፡ የሚገዛለት ሰው፡ የሚጠመድለት ሰው፡ የእግዚአብሔር ቃል እስኪያንቀሳቅሰው ድረስ የማይንቀሳቀስ ሰው አገኘ። ሰዎች ዛሬ፡ እንደዚያ ብቻ ማድረግ ቢችሉ ኖሮ! ከዚያ በኋላ፡ ልክ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር፡ በቀንበር እንደታሰረ፡ እርሱም እስረኛው ሆነ፡ ከ—ከእግዚአብሄር ጋር፡ በፍቅር ቀንበር የተጠመደ የፍቅር እስረኛ ሆነ።

163 ልክ እንደ ጳውሎስ፡ ሁለቱም በተመሳሳይ መንገድ አሰለጠናቸው። ሙሴ የእስራኤልን ልጆች በወታደራዊ ኃይል ለማዳን አሰልጥኖ አወጣው። ጳውሎስን በዚያ ዘመን በዓለም በነበረው በታላቅ መንፈሳዊ ኃይል፡ ከሮማውያን እጅ አስመልጦ ነጻ እንዲያደርጋቸው አሰለጠነው። በገማልያል ሥር በበቀሉ፡ ታላላቅ የሥልጠና ትምህርት ቤቶች ውስጥ።

164 ሁለቱም ወደ በረሃ ወረዱ፣ ኧ—ሀ፡ የተለየ ሰው ሆነው መጡ። ሁለቱም የእሳቱን አምድ አይተዋል። ሁለቱም ነቢያት ነበሩ። አይደል? ሁለቱም፡ ነቢያት ናቸው። ሁለቱም በእሳት አምድ ተነገራቸው፡ ምን ለመሆን፡ ነጻ አውጪ ለመሆን። የእግዚአብሔርን ፈቃድ፡ ለማወቅ በረሃ ሄዱ። መርምረው ለመርዳት፡ ቤታቸውን ሕዝባቸውን እና ሁሉ ረሱ። ትተውም ወደ ምድረበዳ ሄዱ፡ ወደ ምድረበዳ በመሄድ በዚያ ቆዩ። አያችሁ?

165 አንድ አይነት ስልጠና ተሰጣቸው፡ እግዚአብሄር ሁለቱንም ለወጣቸው። እና እነሱ በሚፈልጉት መንገድ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር በሚፈልጋቸው መንገድ መስራት እንዲችሉ፣ ፍጹም እስረኛ መሆን ነበረባቸው። እሱ ትላንትና፣ ዛሬ፣ እና እስከዘላለም ድረስ ያው ነው።

166 ይሄን ለማጠቃለል አስር ደቂቃ ይኖረን ይሆን?

167 ፈጥኜ ወደ ሌላ ገጸ ባህሪ እገባለሁ። አንድ ተጨማሪ በፊቴ ይታየኛል። ስሙም ዮሴፍ ይባላል። የተመረጠ ልጅ ነበር። የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ምሳሌው ነው። ነብይ ሆኖ የተወለደ። ደግሞ፡ ነቢይ የነበረ ነው። እያችሁ? ራዕዮችን የሚያይ ነበርና። ገና ትንሽ ልጅ ሳለ፡ በዙፋን ላይ ተቀምጦ፡ ወንድሞቹም ሲሰግዱለት ራእይ አየ። እያችሁ? አሁን ግን ተመልከቱት። ስለራሱ... ታላቅ ሰው ነኝ ብሎ አሰበ። እያችሁ? እንደሌሎቹ...

168 እግዚአብሄርስ ምን አደረገበት? ለሌሎች ያደረገው ተመሳሳይ ነገር አደረገበት። ምክንያቱ፡ ሙሴ ነጻ አውጪ ነበር፣ ጳውሎስም ነጻ አውጪ ነበር፣ ዮሴፍም ነጻ አውጪ ነበር። ህዝቡን ከረሃብ አድኗልና።

169 እግዚአብሄርስ ምን አደረገበት? ወደ እስር አወረደው፡ በቀጥታ ወደ እስር አወረደው። አዎን፡ ጌታዬ። አስታውሱ፡ በወንድሞቹ ለግብፃውያን ተሸጦ ነበር። እነርሱም ለጲጥፋራ ሸጡት። ጶጢፋራም ትንሽ ነጻነት ሰጥቶት ነበር፡ እና፡ ከዚያ በኋላ፡ የሆነበት የመጀመርያ ነገር፡ የተሰጠው ነጻነት ተወሰደበት። እግዚአብሄር ጨርሶ እስኪገፍፈው ድረስም፡ በእስር ቤት ውስጥ፡ እያለቀሰ፡ ኡኡ እያለ ቆዬ።

170 አሁን አስተውሉ። በዚህ ሁሉ፡ ግን፡ በዚያ፡ በእስር ቤት ውስጥ፡ ሆኖ፡ ጸጋው ከእግዚአብሄር ዘንድ እንደተሰጠው ስለሚያውቅ፡ ወንድሞቹ እንደሚሰግዱለት፡በዙፋኑም እንደሚቀመጥ፡ አስቀድሞ ያየው ራዕይ እንደሚያስላሰል አምናለሁ። እንደሚፈጸምም አስቀድሞ አውቀዋል።

171 ይህ አንድ ነገር ከአእምሮአችን አይጥፋ፡ እንደ እግዚአብሄር ቃል መሰረት፡ በዚህ የዘመን ፍጻሜ የራሱ የሆነች ቤተክርስትያን፡ እና የራሱ ህዝብ ያዘጋጃል። የሰጣቸውን ተስፋዎች ሁሉ፡ አሁን ይፈጽማቸዋል። እኛ እሰራለሁ ብሎ ቃል በገባበት ዘመን፡ እየኖርን ነን። እዚያ ነን። አሁን እውነተኛ እስረኞች ሆነንለት፡ በእርሱ ዘንድ እንድንተሳሰር ይፈልጋል።

172 "በእግዚአብሔር-ዘንድ እታሰራለሁ"? ከእግዚአብሔር ጋር መታሰር እፈልጋለሁ፡ የሚለውን የድሮ መዝሙር ሰምታችሁታል። በጌታ ዘንድ መታሰር ያሰብኩበት፡ አሁን ነው። ሌላ ነገር ሳታደርጉ፡ ጌታ ተንቀሳቀስ ሲል ብቻ፡ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር አድርግ ሲል ብቻ ማድረግ፡ እያችሁ፡ ያኔ ከእግዚአብሔር ጋር መታሰርህ እውን ታደርጋለህ።

173 እሱ የሚያሰበውን፡ አስታውሱ። ስለራሱ የሚያስበው ነገር፡ ፍጹም መውደቁ ነው። እሱ የሚያውቀው ሁሉ፣ የተረዳው ነገር ሁሉ እና፣ ሌላው ሁሉ ጠቅላላ ውድቀት ሆኖበታል። አልሰራለትም። እርሱን ማንም ሊሰማው በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ዘብጥያ አወረዱት። እስር ቤት ገባ። እያችሁ? የማያምኑ ሊያምኑት በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ተወረወረ። ምን ማለቴ እንደሆነ እያችሁ? አገልግሎቱ ምንም ውጤት አላመጣም። ሰዎች ፊታቸውን አዙረውበታል። የሱ አገልግሎት ለማን ይጠቅማል? በማለት በእስር ቤት ውስጥ ምንም ትኩረት አልሰጡትም። በእስር ቤቱ የብረት መዝጊያ አጠገብ ቆሞ ሊሰብካቸው ይችላል፡ ማንም አይሰማውም። እያችሁ? ነገር ግን እስረኛ ሆኖ ቆየ። መንኮራኩሩ፡ በትክክል መሽከርከር እስኪጀምር ድረስ፡ እግዚአብሔር፡ እስረኛ አድርጎ ጠበቀው። "ይሄ ነው ባርያዬ፡" እስኪለው ድረስ። ክብር! ውድቀት ሆነበት!

174 በመጨረሻም፡ እግዚአብሔር፡ ለጳውሎስ፡ እና ለሌሎቹ እንደ ደረሰላቸው ደረሰለት። በእስር ቤቱ ውስጥ ደረሰለት። እርሱን ከእስር ለማስወጣት፡ አስቀድሞ የሰጠውንም ስጦታ ተጠቀመ። ትክክል ነው። ከእስር ቤት አመጣው። ምን አደረገ? ከእስር ቤት እንዳመጣው፡ ከንጉሱ ጋር፡ ከበታቹ ሆኖ ከጎኑ ይቀመጥ ዘንድ፡ በንጉሱ፡ ስልጣን ተሰጠው። እሱ የሚሰጠው ትዕዛዝ ሁሉ፡ እንዲፈጸም፡ ንጉሱ ከእስር ቤት አምጥቶ፡ ስልጣን ሰጠው። አሜን።

175 በእስር ቤት ውስጥ ሳለ ግን ለዓላማ እንደተወለደ ሳያቋረጥ ያሰላስል ነበር። አንድ ቀን ከንጉሥ ጎን እቀመጣለሁ ይል ነበር። ሌሎቹ ሁሉ ይነበረከኩልኛል ይል ነበር። ካየው ራዕይ የተረዳው ይህ ነውና። አሜን። ነገር ግን ራእዩ ሙሉ በሙሉ ከመፈጸሙ በፊት እስረኛ መሆን ግድ ነበረበት። አሜን። ከዚያ በኋላ ግን ገዥ ሆነ። ከእስር ቤት ወጥቶ፡ እግዚአብሄር በአፉ የሚያኖርለትን ቃል ብቻ እንዲናገር፣ የእግዚአብሄርን ቃል እስረኛ ከሆነ በኋላ፡ እግዚአብሄር በህይወቱ ላይ መስራት ጀመረ።

176 አስተውል፣ ሙሴ የፈርዖንን መኳንንት፣ በራሱ ፈቃድ የማሰር ሥልጣን ነበረው። ኧ-ሀ፣ ኧ-ሀ። የፈርዖንን መኳንንት የማሰር ኃይል ነበረው። "ይህን ተራራ 'ተንቀሳቀስ፡' ብትሉት።" ዲያቆናትም ይሁኑ፣ ወይም ፕሪስባይተሮች፣ ወይም—የግዛቱ ዋና ተወካዮችም ይሁኑ ወይም ምንም ይሁኑ። "አስሬሃለሁ፡" ካላቸው፡ ይታሰራሉ። እውነቱ ይህ ነበር። ደስ ያሰኘውን፡ በቃሉ ማድረግ ይችላል። ኣሜን። ክብር ለእግዚአብሔር!

ኦህ፣ ገና ሦስት ደቂቃ ያህል ይኖረኛል፣ ቃሌን እጠብቃለሁ።

177 አሁን እንደተረዳነው፡ የዓለም እስረኛ ከመሆን—የእግዚአብሄር እስረኛ ሆነ። ከ... ጳውሎስም፡ ያው ነው። ሙሴም፡ ያው ነው፡ ከራስ አስተሳሰብ እስር፡ ወደ እግዚአብሄር እስር ወጣ። በወጣም ጊዜ፡ የእግዚአብሄር ስልጣን ይዞ ወጣ። ጳውሎስ በነበረ ጊዜ... ሙሴ የግል አሳቡን፣ ካሰማረከ፣ እና ከገፈፈ በኋላ፣ የክርስቶስን ቃል እስረኛ ሆነ። ወደ ወሰደው ብቻ ይሄዳል...

ያልከው "ስለ ክርስቶስ፡" ነውን?

178 "እዋን ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ መረጠ።" ስለዚህ ልክ እንደ ጳውሎስ እሱም የክርስቶስ እስረኛ ነበር።

179 ሦስቱም ነቢያት እንደ ነበሩ፡ አትርሱ። አያችሁ? ለእግዚአብሔር ፈቃድ እና ለስራው እስረኛ ለመሆን ከራሳቸው አስተሳሰብ መላቀቅ ነበረባቸው።

180 ስለዚህ፡ አሁን፡ በቃሉ ትዕዛዝ፡ የማሰር። በቃሉ ትዕዛዝ የመፍታት ስልጣን እንደነበረው፡ እናስታውሳለን። "በንጉሴ ስም፡ ፈትቻችኋለሁ፡" እስከሚላቸው ድረስ። ፈርዖን ዮሴፍን ልጁ አደረገው። አሜን።

181 ክርስቶስም፡ ልጆቹን፡ የፍቅር እስረኞቹን፡ ያደርጋቸዋል። ያንኑ ስልጣኑም፡ ይሰጣቸዋል። ዮሐንስ 14:12፡ አያችሁ፡ "በእኔ የሚያምን ሁሉ፡" "እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል። ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል።" ስለዚህ የክርስቶስ ፍቅር እስረኛ፡ በንጉሱ በክርስቶስ ስልጣን ይሾማል። አሜን። "እውነት እላችኋለሁ፡ ይህን ተራራ 'ተወርወር' ብትሉት፡ በልባችሁም ባትጠራጠሩ፡ ነገር ግን ያላችሁት እንደሚፈጸም ብታምኑ፡ ይሆንላችኋል። በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፣ ቀንበሬን ከተሸከማችሁ፡" እርሱና ቃሉ አንድ

ናቸውና። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ቃል ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ። ትላንትና፣ ዛሬ እና ለዘላለም ያው ነው! በእኔ ብትኖሩ፤” እዚህ እና እዚያ ሳይሆን፣ “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ፡ የምትፈልጉት ጠይቁ፡ ወይም የምትፈልጉት ተናገሩ፡ ይደረግላችኋል።” ዮሴፍም ስልጣን ተሰጥቶታል።

182 አስታውሱ፡ ከመውጣቱ በፊት፡ ተወስዶ መላጨት ነበረበት። ንጉሱን ከማግኘቱ በፊት ጥቂት ነገሮቹ መላጨት ነበረባቸው። አያችሁ?

183 አንዳንድ ጊዜ፡ እግዚአብሔርም ህዝቡን እንደዛ አውጥቶ፣ ማድረግ የፈለጉትን ሁሉ ማድረግ እንደማይችሉ ለማሳየት፣ ወስዶ ጥቂት የግል ፈቃዳቸውን ይላጭባቸዋል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ አውቃችኋል። ማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ—ለማድረግ ነፃነት የላቸውም። ወደ ሙሉ ሥልጣን ከመምጣታቸው በፊት እና የክርስቶስ የፍቅር-ባሪያ ከመሆናቸው በፊት፡ ተላጭተው መቅረብ አለባቸው። አንዳንድ ጊዜ ያንን ለማድረግ፡ ይላጫቸው ዘንድ፡ ወደ በረሃ ይወስዳቸዋል። ከዚያም እንዲሆኑለት የመረጣቸው ዓላማ እንዲፈጽሙ፡ ከተቀቡት መካከል አርጎ ቀብቶ ያመጣቸዋል። ምን ለማለት እንደፈለግኩ ገብቷችኋል?

ወንድሞች ሆይ፡ የመጨረሻው ዘመን ላይ ነን።

184 በሌሎች ጊዜያት ሁሉ፡ ያደረገውን አስታውሱ። ሁል ጊዜ አንድን ሰው ለመጠቀም ወስዶ የራሱ የሆነውን ነገር አስጥሎ እስረኛው ያደርገዋል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ እግዚአብሔርን ለመከተል፡ የሚያውቀውን ሁሉና፣ ልምምዶቹም፡ ሌላው ሁሉ መርሳት ይጠበቅበታል።

185 የሰውን እና፡ የእግዚአብሔርን ስራ፡ እርስ በርስ ስለሚቃረኑ። ሁለቱን በተመሳሳይ ጊዜ፡ መከተል አይቻልም። በተመሳሳይ ሰዓት ወደ ምስራቅ እና ወደ ምዕራብ መሄድ አትችሉም። በተመሳሳይ ጊዜ ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ መራመድ አትችሉም። በተመሳሳይ ጊዜ ትክክል እና ስህተት መስራት አትችሉም። በአንድ ጊዜ ሰውን እና እግዚአብሔርን መከተል አይቻልም። አይቻልም፡ ወንድሜ። እግዚአብሔርን ትከተላለህ ወይም ሰውን ትከተላለህ።

186 እንግዲህ፡ እግዚአብሔርን የምትከተል ከሆነ፡ ራስህንም ለእግዚአብሔር ከአስገዛህ፣ እንግዲያውስ ለዚያ አምላክ፣ ለዚያ ቃል፣ ለዚያ ፈቃድ እስረኛ ሆነሃል። ሌላው ምንም ቢል፣ ለእሱ—እስረኛ ትሆናለህ።

187 ስሙኝ። በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ስለዚህ በቀሩን ሁለት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ይህንን በአክብሮት እና በትህትና እናገራለሁ። ተመልከቱ። እንደ እኔ አስተያየት፡ ጌታ በዚህ መጨረሻው ዘመን የሚያደርገው፡ እና ማድረግ ያለበት፡ እና የሚያደርገው አንድ ነገር፡ የመኸሩን መሳሪያ መፈለግ ነው። ወለሉን ለማጥራት፡ መሳሪያ ይፈልጋል። ማንኛውም ገበሬ፡ ምርትን ለማፈስ ሲወጣ፡ የሚሠራበት መሣሪያ ይይዛል፡ በርግጥ እህሉን ለመውቃት፡ አንዳንድ መሳሪያ ሊኖረው ይገባል፡ ስለታም ማጭድ፡ ወይም የሆነ ነገር ሊኖረው ይገባል። አሁንም መኸሩ ደርሷል።

188 እግዚአብሔር ሆይ በእጅህ ውሰደን። የፍቅርህ-ባሪያዎች አድርገን። ዛሬ እየኖርንበት ወዳለው ወደዚች ኃጢአተኛ፡የተረገመ ምድር፡ ኢየሱስ ክርስቶስ

ትናንትም ዛሬም እስከ ለዘላለምም ያው፣ እንደሆነ፡ ግንዛቤን ለማምጣት፡ እኛን እንደ መሳሪያ ተጠቀም።

189 ለራሴ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ እስረኛ ልሁንልህ። ወንድሞቼ ሁሉ፡ ጓደኞቼ ሁሉ ቢክዱኝ፡ በመንፈስ ቅዱስ ለቃሉ ቀንበር ተገዢ እሆን ዘንድ፣ መንፈስ ቅዱስ፡ ይፈጸማል ብሎ በተናገራቸው ተመሳሳይ ነገሮች፡ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያረጋግጥ ለማየት የኢየሱስ ክርስቶስ እና የቃሉ እስረኛ መሆን እፈልጋለሁ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ መሆን እፈልጋለሁ።

እንጸልይ።

190 ዛሬ ማታ፣ እኔ የሚገርመኝ፣ አንገታችንን ደፍተን፣ ያለብንን ሌላ የመሆን፣ ራእይ፣ ምናልባትም ራስ ወዳድ የሚያደርጉን፡ የምንወዳቸው ነገሮች፡ ዛሬ ወደ ጎን ማድረግ ካልቻልን እገረማለሁ።

191 ዛሬ፡ አንድ ወጣት ልጅ ተነስቶ፣ ዙሪያውን በማየት፣ “እኔ ሳድግ እንዲህ እሆናለሁ፡ ትልቅ ሰሆን፡ **እንዲህና-እንዲያ** እሆናለሁ ቢል እገረማለሁ።” የጌታ ፈቃድ በህይወታችሁ ሲንቀሳቀስ አይታችሁ፡ እንዲህ ካላችሁ እገረማለሁ፣ “አይ፡ አይ፡ ኧ-ሀ፣ ሀ-ኧህ። እኔ—እኔ... ምኞቴ ሁሉ ጠፍቷል። ላለፉት ጥቂት ቀናቶች፡ መንፈስ ቅዱስ ተናግሮኛል። በዚህ በመጨረሻው ዘመን፡ የመከር መሳርያው ለመሆን፡ ህይወቴን ለእግዚአብሄር አ—አ—አሳልፌ—መስጠት እፈልጋለሁ።”

192 ጥሩ የቤት እመቤት ሰነ ምግባር ሊኖራት የምትመኝ አንድ ወጣት ልጃገረድ፣ ወይም—ደግሞ በጣም ቆንጆ ትንሽ ኮረዳ፡ ምናልባት አንድ ቀን ሆሊውድን ሰራሽ ለማድረግ የምታስቢ፡ ዛሬ—በህይወትሽ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለመስማት እና ራእይሽን በእግዚአብሔር ህልውና ፊት ለመጣል፣ ፈቃደኛ ካልሆንሽ እጅግ እገረማለሁ። እግዚአብሔር ማን እንደሆንሽ ያውቃል።

193 በቤተክርስትያን ውስጥ የቅርብ አገልጋይ፣ ወይም አገልጋይ፣ ወይም ሰራተኛ ይኖር ይሆን ወይ ብዬ እሰባለሁ። እኔ ወደዚህ የምመጣው፣ አልፎ አልፎ ነው። ዛሬ ማታ፡ እዚህ ካሉ ሰዎች አንድ-ሶስተኛም—አላውቃቸውም፡ ይሁን እንጂ... ከጥቂቶቹ መካከል። ጨክኖ እንዲህ የሚል አንድ ሰው፡ ይኖር ይሆን ብዬ እሰባለሁ፣ “ማንም ምንም ይበል አይገደኝም። ከአሁን በኋላ የእግዚአብሄር ባርያ ነኝ። ምንም—ይምጣ—ምን፡ ቃሉን እሰብካለሁ። ድርጅታችን—እንደፈለገ ቢፈርጀኝም፡ አይገደኝም፡ እኔ ግን ከቃሉ ጋር እጸናለሁ። እኔ—አደርገዋለሁ። የእኔ ፈቃድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ የእኔ ፈቃድ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኛ እሆናለሁ። በጸጋ እና በረድኤቱ፡ አደርገዋለሁ።”

194 አንገታችንን ደፍተን ሳለን፡ እስቲ አስቡት። ዛሬ ማታ ስንቶቻችሁ ያንን ዓይነት ራእይ አላችሁ? እጆች ይነሱ። እኔም፡ እንደ እናንተ። በሙላት እማረካለሁ። አንገታችንን ደፍተን አሁን፣ ማለቁን እያሰብን፡ ቀስ እያልን፣ በጸሎት መንፈስ ሆነን።

እማረካለሁ፡<br>
እማረካለሁ፡<br>
ሁሉም ለአንተ፡ ብሩክ መድሓኒቴ፡<br>
እማረካለሁ፡

እማረካለ-...

195 ከልባችሁ ነው? “እሰረኛው መሆን ፈልጌአለሁ።”

እኔ...

“ውሰደኝ፡ ጌታ ሆይ። ዛሬ ማታ፡ ወደ ሸክላ ሠሪ ቤት ውሰደኝ። ሁለንተናዬን ሰብረህ፣ እንደገና ቅረጸኝ... ? ... ”

... ለአንተ፡ ብሩክ መድሓኒቴ፡
እማረካለሁ።

196 የሰማይ አባት ሆይ፣ መዝሙሩ መጫወቱን እንደቀጠለ፣ መዝሙሩን አቋርጬ—ከአንተ ጋር ለአፍታ መነጋገር፡ እጅግ የሚበልጥ እንደሆነ አሰቤአለሁ። ሰዎች ሁሉ “በሙላት እማረካለሁ፡” ብለው እያሰቡ፡ አባት ሆይ፡ የመጨረሻው ዕድል መሆኑን እያሰብን እንድናደርግ እርዳን። እራሳችንን ሰአንተ ለማስማረክ፡ ወደ ጌታ ገበታ፡ በትህትናና ሰንመጣ፣ ልብሳቸውን እንዳጠቡ፣ ነፍሳቸውን፣ ፈቃዳቸውን፣ ምኞታቸውን እንዳጠቡ፣ ሰዎች ሆነን እንቀርብ ዘንድ እርዳን።

197 ጌታም ቃሉን ያምጣና፡ ከእግዚአብሄር ቃል፡ ከቀንበሩ ጋር ያስተሳሰረን። መንፈሰ ቅዱሰም፡ ቀንበሩ ከልባችን ጋር ሲተሳሰር እየሰማን ባለንበት፡ አሁን ይውሰደን፣ “ከዛሬ ምሽት ጀመሮ፡ እንደ ቃልህ ተቀብዬሃለሁ። ከአሁን በኋላ የራሰህን አሳብ አታሰብም። እኔ የማሰበውን አሳብ ታሰባለህ። ፈቃዴን ትሞላለህ። እመራሃለሁ ይበለን።” እግዚአብሔር ሆይ፣ ለእያንዳንዳችን ልምድ እንዲሆን ይህን ሰጠን።

198 ባል እና ሚሰት የሆኑ፡ ገናም ባልና ሚሰት ሊሆኑ የተዘጋጁ፡ ወጣቶች እዚህ ተቀምጧል። መሄጃቸው የደረሰ፡ ሽማግሌዎች፡ አገልጋዮች ተቀምጧል። እና፣ ጌታ ሆይ፣ እነሆ ወንድም ኔቪል፣ እና እኔ፣ የመሳሰልን አሰላሉን ወጥተናል። ቀሪ ቀናችን የሚቆጠር ሆነናል። እርምጃዎቻችን ከድሮ ይልቅ በበለጠ ጥንቃቄ መራመድ ጀምረናል። የምንረግጠውን መጠንቀቅ ጀምረናል። በሰጋዊ አነጋገር፡ እንደ ድሮአችን፡ ተማምነን መርገጥ-ተሰኖናል። ነገር ግን፣ ጌታ ሆይ፣ ሟች ህይወት እየጠፋ እንደሆነ ሰናይ፣ አንተ እጃችንን ሳትይዘን፡ አንዳችም በእግራችን የምነረግጠው እርግጠኛ አይደለንም።

199 አሁንም፡ አምላኬ ሆይ፡ ውሰድን፡ ትወሰደናለህ? ልባችንን እና ፈቃዳችንን ውሰድ፡ በዚህ ምሽት፡ ለቃሉ፡ ለክርሰቶሰ፡ እሰረኛ እንሁን። አምላካዊ ሕይወት እንኑር። እነዚህ ሴቶች፡ እነዚህ ወጣት ሴቶች፡ እነዚህ ወጣቶች፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፡ ጌታ ሆይ፡ ሕይወታቸውን ያሰማርኩ። ራእያቸው ኢየሱሰ ክርሰቶሰን የማገልገል ራእይ ይሁን። እኛም የመለኮታዊው ጸጋ እና ፈቃድ እሰረኛ እንሁን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

200 እኔ መሰራት የምችለው፡ የማውቀውን ይህ ብቻ ነው፡ ጌታ ሆይ። እነዚህ ትንሽ የተበታተኑ-ቃላቶቼ፡ በትክክል እንደምታሰቀምጣቸው—አምናለሁ። እጅግ ብዙ ሙቀት አለና፡ ምንም እንኳን ሰዎች መሰማት ቢፈልጉም፡ እጅግ ይሞቃልና። ብዙዎቹ ማልደው ወደ ሥራ ይሄዳሉና ወደ ቤታቸው መሄድ አለባቸው። ብቻ አንተ “እሰረኛ፡” ዘር በልባቸው ውሰጥ አኑር።

201 ዛሬ ከሰዓት፡ ወይም ማታ ወደ ቤታቸው ሄደው፡ ለጸሎት ሲዘጋጁ... ሚስቶቻቸውን ሲያናግሩ፡ ወይም አልጋቸው ላይ ወጥተው፡ አይን ለአይን እየተያዩ፡ “ውዴ፡ የዛሬ ጉባኤ፡ እንዴት ነበር? በእውነት የክርስቶስ እና የፈቃዱ እስረኞች ሆነናል፡ ወይስ—ወይስ የምንሠራው በራሳችን ፈቃድ ነው? ”

202 ወጣት ወንዶች እና ወጣት ሴቶች፡ በየቦታው በተለይም፡ ዛሬ ማታ፡ መልእክቱን የሰሙት ሁሉ፡ ተመሳሳይ ጥያቄ ራሳቸውን ይጠይቁ። “የራሴን ሕይወት ትቼ፡ እስረኛ ለመሆን ፈቃደኛ ነኝን ይበሉ? ”

203 “ነፍሱን የሚያድን ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ግን ያገኛታል።” አባት ሆይ፡ እስረኛህ መሆን፡ እንዲህ እንደሆነ፤ እኛ እናውቃለን፣ ይህም ምኞታችንን እና የግል ፍላጎታችንን በመተው፡ የአንተን መፈለግ ነው፡ ያን ጊዜ የዘለአለም ህይወት ይኖረናል። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

204 አሁን እኔ የማውቀው ነገር ቢኖር፡ በእጅህ አሳልፎ መስጠት ብቻ ነው። እና ለመጨረሻው-ቀን መከር የሚሆኑ ምርጥ መሳሪያዎች የሚያፈራ ታላቅ—ፍሬ ይሁን፣ ወንዶችና ሴቶች፣ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ እየተገዙ፣ ለክርስቶስ በመለኮታዊ ፍቅር እስራት የታሰሩ፣ ለፍቅሩ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ እስረኞች ይሁኑ። በሰሙ እንጠይቃለን።

እማረካለሁ፡

እንቁም።

እማረካለሁ፡
ሁሉም ለአንተ፣ የኔ... ? ...

205 ዓይኖቻችንን ጨፍነን እና እጆቻችንን ወደ ላይ በማድረግ፡ ደግመን እንበለው።

እማረካለሁ፡
እማረካለሁ፡
ሁሉም ለአንተ፡ ብሩክ መድሓኒቴ፡
እማረካለሁ፡

206 አሁን፣ አንገታችንን ጎንበስ አርገን፣ **የኢየሱስን ሰም ከአንተው ጋር ያዝ**፣ የሚል የሰንብት መዝሙር ከመዘመሩ በፊት፣ እዚህ ያለው ወንድም... ሰሙን እረሳሁት—ወደዚህ እንዲመጣ እጋብዛለሁ። ስለ ጨለማው ራእይ የመሰከረችው እህት፣ እሱም እንደተፈወሰ። እና እስታውሱ፣ ወደ ኋላ መለስ ብላ ስትመለከት፣ መጋረጃው የለም። እምነቷ ይህን አደረገ። በጸሎት አሰናብተን፡ ትጸልይልናለህ፡ ወንድሜ? የእግዚአብሄርን በረከት ለምንልን።

**እስረኛው** AMH63-0717

(A Prisoner)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ እሮብ ማታ፡ ሐምሌ 17 ቀን፡ 1963 በዩ/ኤስ/ኤ/፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ከሚገኝ ብራንሃም ተበርናክል፣ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org